## በመንግሥት ፡ የአስተዳደር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ የተወሰኑ ፡ ጉዳዮችን ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ገና ፡ የማየት ፡ በሕገ ፡ መንግሥት ፡ የተደገፈ ፡ ሥልጣን ።

### መነሾ ፡ ጥያቄዎች ፦

ከሮበርት ፡ ሲ ፡ ሚንስ — የሕግ ፡ ፋኩልቲ ።

አዲሱ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ከአስነሳቸው ፡ እስካሁን ፡ መልስ ፡ ካልተገኘላቸው ፡ ጥያቄዎች ፡ መካከል ፡ አንዱ ፤ የሰውን ፡ ሕይወት ፤ ነፃነት ፤ ወይም ፡ ንብረት ፡ ለማሳጣት ፡ የሚቃጡ ፤ በአስተዳደር ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ አፈጻጸም ፡ ረገድ ፡ የተወሰኑ ፡ ጉዳዮችን ፡ ወይም ፡ የተወሰዱ ፡ እርምጃዎችን ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ገና ፡ የማየት ፤ (በፍርድ ፡ ቤት ፡ አስገዳጅነት ፡ ሊፈጸም ፡ የሚችል) ፡ በሕገ ፡ መንግሥት ፡ የተደገፈ ፡ ሥልጣን ፡ መኖርና ፡ አለመኖር ፡ ነው ። "በፍርድ ፡ ቤት ፡ እንደገና ፡ ማየት" ፡ በአዋጅ ፡ ተገልጦ ፡ በታገደበት ፡ ስፍራ ፡ ጥያቄው ፡ ጐልቶ ፡ ይታያል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ አግባብ ፡ ያለው ፡ አዋጅ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ እንደገና ፡ ማየትን ፡ በሚፈቅድበትም ፡ ጊዜ ፡ (ለምሳሌ ፡ እንደገና ፡ የሚታየው ፡ ጭብጥ ፡ የተወሰነ ፡ የሆነ ፡ እንደሆን) ፡ ጥያቄው ፡ መነሣቱ ፡ አይቀርም ።

ይህን ፡ መሳይ ፡ በሕገ ፡ መንግሥት ፡ የተደገፈ ፡ ሥልጣን ፡ ካለ ፡ መገኘት ፡ የሚገባው ፡ በአንቀጽ ፡ ፵፫ ፡[1] ውስጥ ፡ ይሆናል ። የዚህንም ፡ አንቀጽ ፡ ቋንቋ ፡ በመመልከት ፡ አከራካሪው ፡ ጉዳይ ፡ "ሕግ" ፡ የሚለውን ፡ እነጋገር ፡ በዚህ ፡ አግባቡ ፡ በሚገባ ፡ በመተርጐም ፡ ላይ ፡ ሊወሰን ፡ ቢችል ፤ የችግሩ ፡ (የፕሮብሌሙ) ፡ አመራመር ፡ አጭርና ፡ የበለጠ ፡ ቀጥተኛ ፡ በሆነ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ጉዳዩን ፡ ከመ

1 አንቀጽ ፡ ፵፫ ።

ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ሕይወቱን ፡ ነጻነቱን ፡ ወይም ፡ ንብረቱን ፡ ያለ ፡ ሕግ ፡ አያጣም ።

ጉዳዩ ፤ በፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲታይ ፡ የሚል ፡ የሕገ ፡ መንግሥት ፡ መብት ፡ በተጨማሪ ፡ ወይም ፡ በምትክነት ፡ በአንቀጽ ፡ ፷፪(ለ) ላይ ፡ ሊመሠረት ፡ ይቻል ፡ ይሆናል ። በዚህም ፡ አንቀጽ ፡ መሠረት ፡

"በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ነዋሪ ፡ የሆነ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ በተደረገበት ፡ ጉዳት ፡ ምክንያት ፡ በመንግሥቱ ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ሚኒስቴር ፡ በመሥሪያ ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በወኪል ፡ መሥሪያ ፡ ቤትም ፤ ቢሆን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ላይ ፡ ክስ ፡ ሊያቀርብ ፡ ይችላል ።"

በዚህ ፡ አርእስት ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ ከተገለጹት ፡ አከራካሪ ፡ ጉዳዮች ፡ ውስጥ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ለሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ የሰጡት ፡ ትርጉም ፡ የበላይነት ፡ ይኖረው ፡ እንደሆንና ፤ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ቀደም ፡ ብለው ፡ በተደረጉት ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ተመልሶ ፡ ተፈጻሚ ፡ ስለመሆኑ ፡ የተነገሩት ፡ ሁሉ ፤ የአስተዳደር ፡ አድራጎት ፡ ወይም ፡ በአጋጊ ፡ የወጣ ፤ ሕግ ፡ በፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በዳኝነት ፡ መታየት ፡ በአንቀጽ ፡ ፷፪ ፡ (ለ) ከተመሠረተ ፡ ለክርክሩ ፡ አግባብ ፡ ይኖራቸዋል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አንቀጽ ፡ ፵፫ ፡ የተገቢ ፡ የሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ዋስትና ፡ መሆን ፡ አለመሆኑ ፡ በዚህ ፡ ክርክር ፡ ውስጥ ፡ አግባብ ፡ ሊኖረው ፡ አይችልም ፤ ሆኖም ፡ ይህ ፡ አንቀጽ ፡ በሌላ ፡ ረገድ ፡ ሲጠቀስ ፡ ተገቢ ፡ ሆኖ ፡ ሊገኝ ፡ ይችላል ።

ጀመሪያው ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ማቅረብ ፡ ሁለት ፡ ጥያቄዎችን ፡ መሸሽና ፡ ለሦስተ ኛው ፡ ጥያቄ ፡ መልስ ፡ እንደተገኘ ፡ አድርጎ ፡ መቀበል ፡ ይሆናል ። የዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ እነዚህ ፡ "ሕግ" ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ ለመተርጐም ፡ ብቻ ፡ ከተሰነዘረ፡ ክርክር ፡ (በአንዳች ፡ ምክንያት) ፡ ውጭ ፡ የሚቀሩት ፡ መነሾ ፡ ጥያቄዎች ፡ ናቸው ። በነዚህም ፡ ጥያቄዎች ፡ የመጨረሻ ፡ አወሳሰን ፡ መሠረት ፡ (በዚህ ፡ ጽሑፍም ፡ የመጨረሻ ፡ ውሳኔ ፡ አልቀረበም) "በአንቀጽ ፡ ፴፫" ፡ የ"ሕግ" ፡ ፍች ፡ የኢት ዮጵያ ፡ የሕገ ፡ መንግሥት ፡ ሕግ ፡ ዋና ፡ አከራካሪ ፡ ጉዳይ ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ። አለበ ለዚያም ፡ ትርጉሙ ፡ ምን ፡ እንደነበረ ፡ ለማወቅ ፡ ያህል ፡ ብቻ ፡ ለሚደረግ ፡ ግዙፍ ፡ ጥቅም ፡ ለማይሰጥ ፡ የአእምሮ ፡ ክርክር ፡ ማደበሪያ ፡ ምቹ ፡ ነገር ፡ ሆኖ ፡ ይቀራል ።

## <u>የተሸሹት ፡ ጥያቄዎች ፡ የአንቀጽ ፡ ፻፳፪ ፡ ትርጉም ።</u>

በአጋጊ ፡ (በፓርላማ) ፡ የታወጁትን ፡ ሕጎች ፡ አንድ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሕገ ፡ መንግሥትን ፡ በተመረኮዘ ፡ ምክንያት ፡ ለመሻር ፡ ሥልጣን ፡ አለው ፡ ወ ይስ ፡ የለውም ፡ የሚለው ፡ ጥያቄ ፡ ከተሸሹት ፡ ጥያቄዎች ፡ የመጀመሪያው ፡ ይሆናል ። ይህ ፡ ጥያቄ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ በዚሁ ፡ መጽሔት ፡ ገጾች ፡ ውስጥ ፡ በፕሮፌሰር ፡ ክሽችኖቢች ፡[2] ተወስቶአል ። የእሳቸውም ፡ ክርክርና ፡ የደረሱበት ፡ ማጠቃለያ ፡ ሐሳብ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ እንደተመለከተው ፡ በአጭሩ ፡ አለአንዳች ፡ አድልኦ ፡ ሊገ ለጽ ፡ ይቻል ፡ ይሆናል ።

የሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፻፳፪ ፡[3] ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ የኢ ንተርናሲዮናል ፡ ግዴታዎች ፡ ጋር ፡ ባንድነት ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ መሆኑን ፡ ያረጋግጣል ። ወደፊትም ፡ የሚታወጁ ፡ አዋጆችና ፡ ሌሎች ፡ የመንግሥት ፡ ድርጊቶች ፡ ከሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ የማይስማሙ ፡ ሲሆኑ ፡ ዋጋ ፡ የሌላቸውና ፡ የማያገለግሉ ፡ ይሆናሉ ፡ ተብለዋል ። አንቀጽ ፡ ፻፳፪ ፡ የበላ ይነት ፡ አንቀጽ ፡ (ሱፔረማሲ ፡ ክሎዝ) ፡ ተብሎ ፡ ከሚታወቀው ፡ የተባበሩት ፡ የአ ሜሪካ ፡ መንግሥት ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ጋር ፡ ይመሳሰላል ። በሚለያዩበትም ፡ ስፍራ ፡ የአንቀጽ ፡ ፻፳፪ ፡ አነጋገር ፡ ይበልጡኑ ፡ የጠነከረና ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ ነው ። የተባበሩት ፡ የአሜሪካን ፡ መንግሥትን ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በየአንዳንዱ ፡ ግዛት ፡

---

2 ጂ ፡ ክሽቼኖቢች ፡ "የሕጎች ፡ የበላይና ፡ የበታች ፡ ደረጃ ፡ በኢትዮጵያ" ፡ <u>የኢት ፡ ሕግ ፡ መጽሔት</u> ፡ ፩ኛ ፡ ቦሊዩም ፡ ቊጥር ፡ ፩ ፡ (፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም) ፡ ገጽ ፡ ፻፲፩ ።

3 አንቀጽ ፡ ፻፳፪ ፡—

"ይህ ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተካፋይ ፡ ከምትሆንባቸው ፡ ከኢንተር ናሲዮናል ፡ ውሎች ፡ ከዓለም ፡ ስምምነቶችና ፡ ግዴታዎች ፡ ጋራ ፡ በአንድነት ፡ ሆኖ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ ይሆናል ፡ ወደፊትም ፡ የሚሠሩ ፡ ሕጎች ፡ ድንጋጌዎች ፡ ፍርዶች ፡ ውሳኔዎች ፡ ሁሉ ፡ ከዚህ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ የማይስማሙ ፡ ሲሆኑ ፡ ዋጋ ፡ የሌላቸውና ፡ የማያገለግሉ ፡ ይሆናሉ ።"

4 የዩናይትድ ፡ ስቴትስ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፮ ፡ ፪ኛው ፡ ክፍል ፡—

"ሕገ ፡ መንግሥቱና ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ መሠረት ፡ የሚወጡ ፡ የተባበረው ፡ የአሜሪካ ፡ መንግሥት ፡ ሕጎች ፡ እንዲሁም ፡ በተባበረው ፡ የአሜሪካ ፡ መንግሥት ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ የተፈ ጸሙ ፡ ወይም ፡ ወደፊት ፡ የሚፈጸሙ ፡ የመንግሥታት ፡ ስምምነቶች ፡ ሁሉ ፡ የሀገሪቱ ፡ የበ ላይ ፡ ሕግ ፡ ይሆናሉ ፡ በያንዳንዱ ፡ ግዛት ፡ የሚያስችሉ ፡ ዳኞችም ፡ ተቃራኒ ፡ የሆነ ፡ የግዛቱ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ወይም ፡ ሕግ ፡ ሳያግዳቸው ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ይመራሉ ።"

(ስቴት) ፡ የታወጁትን ፡ ሕጎች ፡ ለመሻር ፡ ያስቻላቸው ፡ ሥልጣን ፤ [5] ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ መሠረት ፡ ይህ ፡ "የበላይነት ፡ አንቀጽ" ፡ ስለሆነ ፤ በመጀመሪያ ፡ ሲመለከቱት ፤ አንቀጽ ፡ ፻፳፪ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶችም ፡ አጋጊ ፡ ባወጃቸው ፡ ሕጎች ፡ ላይ ፡ ተመሳሳይ ፡ ሥልጣን ፡ አላቸው ፡ የሚያሰኝ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ የሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ ፍች ፡ ለመተርጐም ፡ ለዳኞች ፡ የበላይነትን ፡ ላስገኘው ፤ የተባበሩት ፡ የአሜሪካን ፡ መንግሥት ፡ እምነት ፡ ሁለተኛ ፡ ሥረ ፡ ነገር ፡ የሆነው ፤ የሥልጣን ፡ በዳኝነት ፤ በፓርላማና ፤ በአስተዳደር ፡ የመንግሥት ፡ ባላዎች ፡ (ቅርንጫፎች) ፡ መካከል ፡ መከፋፈል ፤ በኢትዮጵያ ፡ የለም ። ማንኛውም ፡ ሕግ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ከመዋሉ ፡ በፊት ፡ ፈቃድ ፡ በሚያስፈልገው ፤ ብቻውን ፡ ሕግ ፡ ለማውጣት ፡ ሥልጣን ፡ ባለው ፤ የመጨረሻ ፡ ይግባኝ ፡ ሰሚ ፡ ፈራጅና ፡ የመጨረሻውም ፡ የበላይ ፡ አስተዳዳሪ ፡ በሆነው ፤ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ አካል ፤ ሦስቱ ፡ የኢትዮጵያ ፡ የመንግሥት ፡ ባላዎች ፡ (ቅርንጫፎች) ፡ ቁጥጥሮአቸው ፡ ላይ ፡ ይገናኛሉ ። ስለዚህ ፡ ለአንድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ በሆነ ፡ ምክንያት ፡ አጋጊ ፡ ያወጀውን ፡ ሕግ ፡ ዋጋ ፡ አልባ ፡ እንዲሆን ፡ ማድረግ ፤ ፍሬ ፡ ቢስና ፡ ምናልባትም ፡ ከኢትዮጵያ ፡ የመንግሥት ፡ አቅዋም ፡ መሠረታዊ ፡ ጠባይ ፡ ጋር ፡ ተቃራኒ ፡ ይሆናል ፤ በማለት ፡ ፕሮፌሰር ፡ ክሽችኖቢች ፡ ሐሳባቸውን ፡ ያጠቃልላሉ ።

እዚህ ፡ ላይ ፡ ፕሮፌሰር ፡ ክሽችኖቢች ፡ እንደ ፡ ተመለከቱት ፡ ሁሉ ፤ አጋጊ ፡ ያወጀውን ፡ ሕግ ፡ ዋጋ ፡ አልባ ፡ የማድረግን ፡ ሥልጣን ፤ በአንድ ፡ የተለየ ፡ ጉዳይ ፡ (ክስ) ፡ ላይ ፡ አጋጊ ፡ ያወጀውን ፡ ሕግ ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ በሆነ ፡ ምክንያት ፡ ከመሻር ፡ ሥልጣን ፤ መለየት ፡ ያሻል ። ፕሮፌሰር ፡ ክሽችኖቢችም ፡ ከፊተኛው ፡ ቀለል ፡ ያለ ፡ በሆነው ፤ በኋለኛው ፡ ሥልጣን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ እንደሚገባ ፡ ሊጠቀሙበት ፡ የሚቻል ፡ መሆኑን ፡ ወደ ፡ ጐን ፡ አልተውም ። ክርክራቸውም ፡ የፍርድ ፡ ቤቶችን ፡ በዚህ ፡ ሥልጣን ፡ መጠቀም ፡ ብልህ ፡ ሐሳብ ፡ መሆንና ፡ አለመሆኑን ፡ እንደ ፡ መመልከቱ ፡ መጠን ፤ አጋጊ ፡ ያወጀውን ፡ ሕግ ፡ ዋጋ ፡ አልባ ፡ ለማድረግ ፤ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ያለውን ፡ ሥልጣን ፡ ስለማይመለከት ፡ ይህን ፡ አማካይ ፡ መንገድ ፡ አለአንዳች ፡ የሐሳብ ፡ አሰካክ ፡ መቃወስ ፡ ሊዘሉት ፡ ችለዋል ። ለክርክራቸው ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ ከመሞከር ፡ በፊት ፡ ግን ፡ ጥያቄው ፡ የሚመለከተው ፡ የፍርድ ፡ ቤትን ፡ ሥልጣን ፡ ከሆነ ፡ አማካዩ ፡ መንገድ ፡ ላይኖር ፡ የሚችል ፡ መሆኑን ፡ ማስተዋል ፡ ይጠቅማል ። በዚህ ፡ ረገድ ፤ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ በሆነ ፡ ምክንያት ፡ እንደ ፡ አዋጅ ፡ እንዳይሠራበት ፡ የሚያደርግ ፡ የዳኝነት ፡ ውሳኔ ፡ በተከራካሪዎቹ ፡ መካከል ፡ ብቻ ፡ የሚጸና ፡ ቢሆን ፤ ወይም ፡ የተባለውን ፡ አዋጅ ፡ ዋጋ ፡

---

5 ማክሎች ፡ ከሚሪላንድ ፡ ሕግ ፡ አስከባሪ ፡ ጋር ፡ በተካሰሱበት ፡ (የተባበረው ፡ የአሜሪካ ፡ መንግሥት ፡ ጠቅላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፲፰፻፲፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ) ፡ ዊትን ፤ ፬ኛ ፡ ቮሉዩም ፤ ገጽ ፡ ፫፻፲፮ ፤ ሎውየርስ ፡ ኤድ ፡ ፬ኛ ፡ ቮሉዩም ፤ ገጽ ፡ ፭፻፸፱ ፡ ይመለከቷል ። ስለሆነም ፡ የፌዴራል ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ጋር ፡ የሚቃረንን ፡ የፌዴራል ፡ ሕግ ፡ ለሚሰጥበት ፡ ሥልጣን ፡ መሠረት ፡ ይህ ፡ አይደለም ። የሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ የበላይነት ፡ የመሠረተው ፡ አንቀጽ ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ መሠረት ፡ የሚወጡ ፡ የተባበረው ፡ የአሜሪካ ፡ መንግሥት ፡ ሕጎች ፡ ብቻ ፡ የበላይነት ፡ አላቸው ፡ ቢልም ፡ እንኳ ፡ ከሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ጋር ፡ የሚቃረኑ ፡ የፌዴራል ፡ ሕጎች ፡ አቋም ፡ ተተንትኖ ፡ አልተወሰነም ፤ የፌዴራል ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ከሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ጋር ፡ የማይስማሙ ፡ የፌዴራል ፡ ሕጎችን ፡ ዋጋ ፡ የማሳጣት ፡ ሥልጣን ፡ አላቸው ፡ ተብሎ ፡ መጀመሪያ ፡ ውሳኔ ፡ የተሰጠበት ፡ ክስ ፡ ማርበሪና ፡ ማድሰን ፡ የተካሰሱበት ፡ (የተባበረው ፡ የአሜሪካ ፡ መንግሥት ፡ ጠቅላይ ፡ ፍ/ቤት ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ ፲፰፻፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ክራንች ፡ ቮሉዩም ፡ ፩ ፡ ገጽ ፡ ፻፴፯ ፡ ሎውየርስ ፡ ኤድ ፡ ቮሉዩም ፡ ፪ ፡ ገጽ ፡ ፷) ፡ ስለ ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ የበላይነት ፡ የተደነገገውን ፡ አንቀጽ ፡ አይጠቅስም ። በዚህ ፡ ክስ ፡ ውሳኔ ፡ ቺፍ ፡ ጀስቲስ ፡ ማርሻል ፡ የሰጡዋቸው ፡ ምክንያቶች ፡ (፩) በጽሑፍ ፡ የወጣ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ የበላይነት ፡ ጠባይ ፡ አለው ፡ (፪) ስለዚህ ፡ ከሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ጋር ፡ የማይስማማ ፡ ተራ ፡ ሕግ ፡ ዋጋ ፡ የለውም ፡ (፫) ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ዋጋ ፡ በሌላቸው ፡ ሕጎች ፡ አይመሩም ፡ የሚሉ ፡ ነበሩ ።

የሌለውና ፡ የማያገለግል ፡ የሚያደርገው ፡ ቢሆን ፡ ምንም ፡ ልዩነት ፡ አያመጣም ። በሁለቱም ፡ መንገድ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሚያረጋግጠው ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ በአዋጅ፡ ከወጣ ፡ ሕግ ፡ በላይ ፡ መሆኑንና ፡ የሕገ ፡ መንግሥቱንም ፡ ፍች ፡ ለመተርጐም ፡ ከአጋጊው ፡ ይልቅ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በላይነት ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ ነው ። ሁለቱ ፡ ሁናቴዎች ፡ የሚለያዩት ፡ ፍርድ ፡ በሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ቤትና ፡ በሌሎች ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ መካከል ፡ ባለው ፡ ግንኙነት ፡ ላይ ፡ ነው ። በውሳኔ ፡ ጸንቶ ፡ የመገኘት ፡ እምነት ፡ ተቀባይነትን ፡ ያገኘ ፡ እንደሆነና ፡ በበላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤትም ፡ የተወሰነ ፡ ሕጋዊ ፡ ደንብ ፡ በዝቅተኛው ፡ ላይ ፡ እንዲጸና ፡ ሆኖ ፡ የፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የበላይና ፡ የበታች ፡ እርከን ፡ ውስጥ ፡ ባለው ፡ ደረጃ ፡ መጠን ፡ አዋጁን ፡ ዋጋ ፡ አልባ ፡ ሊያደርገው ፡ ይችላል ።

በሌላ ፡ አነጋገር ፡ ደግሞ ፡ ለሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ በዳኝነት ፡ የተሰጠው ፡ አገላለጽ ፡ (ትርጉም) ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ ከሆነ ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ በሆነ ፡ ምክንያት ፡ አዋጅን ፡ ዋጋ ፡ አልባ ፡ ለማድረግ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሥልጣን ፡ ሊኖረውም ፡ ላይኖረውም ፡ ይችላል ። ይህ ፡ የሚወሰነው ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ደረጃ ፡ አቅዋምና ፡ በውሳኔ ፡ ጸንቶ ፡ የመገኘት ፡ እምነት ፡ ተቀባይነት ፡ እንደ ፡ ማግኘቱና ፡ እንዳለማግኘቱ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ለሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ በዳኝነት ፡ የተሰጠው ፡ ትርጉም ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ ካልሆነ ፡ በሁለት ፡ ተከራካሪዎች ፡ መካከል ፡ እንዳለ ፡ የሕግ ፡ ጉዳይ ፡ እንኳን ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በአጋጊ ፡ የታወጁ ፡ ሕጎችን ፡ ለመሻር ፡ ሥልጣን ፡ የለውም ። በፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሥልጣን ፡ ረገድ ፡ ሲታይ ፡ አንድ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ በሆነ ፡ ምክንያት ፡ አዋጆችን ፡ እንዲሽር ፡ የሚፈቀደው ፡ ግን ፡ ውሳኔው ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ከቀረበው ፡ ጉዳይ ፡ (ክስ) ፡ ወዲያ ፡ እንዳያልፍ ፡ የሚያደርግ ፡ አስታራቂ ፡ ውጤት ፡ ሊገኝ ፡ የሚቻለው ፡ ለሦስቱም ፡ አከራካሪ ፡ ጉዳዮች ፡ ለያንዳንዳቸው ፡ የሚከተለውን ፡ አንድ ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ የተቻለ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡— ማለት ፡ ለሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ በዳኝነት ፡ የተሰጠው ፡ አገላለጥ ፡ (ትርጉም) ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ መሆን ፡ አለበት ፡ አንድ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀደም ፡ ብለው ፡ በቀረቡለት ፡ ጉዳዮች ፡ ራሱ ፡ በፈረደው ፡ ፍርድ ፡ እንዲጸና ፡ መገደድ ፡ የለበትም ፡ እንዲሁም ፡ ዝቅተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ከፍ ፡ ባሉ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በተሰጡ ፡ ውሳኔዎች ፡ መሠረት ፡ እንዲፈርዱ ፡ መገደድ ፡ የለባቸውም ፡ ማለት ፡ ይኖርብናል ።

ታዲያ ፡ ለሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ በዳኝነት ፡ የተሰጠው ፡ አገላለጽ ፡ (ትርጉም) ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ ነውን ? ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ራሱ ፡ ይህ ፡ የበላይ ፡ ሕግነት ፡ ደረጃ ፡ እንዳለው ፡ በአንቀጽ ፡ ፻፳፪ ፡ ግልጽ ፡ ነው ። ምንም፡ እንኳን ፡ አንቀጽ ፡ ፻፳፪ ፡ ራሱ ፡ የሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ ትርጉም ፡ ማን ፡ መወሰን ፡ እንደሚገባው ፡ ባይናገር ፡ አንቀጽ ፡ ፻፲ ፡ ይህን ፡ ኀላፊነት ፡ ለፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የሰጠ ፡ ይመስላል ።

"ዳኞች ፡ በሕግ ፡ መሠረት ፡ ሲያነጋግሩና ፡ ፍርድ ፡ ሲሰጡ ፡ ነጻ ፡ (ኢንዲፔንዳንት) ፡ ናቸው ፤ የፍርድ ፡ ሥራን ፡ በሚሠሩበትም ፡ ጊዜ ፡ ከሕግ ፡ በቀር ፡ በሌላ ፡ ሥልጣን ፡ አይመሩም ።"

የአንቀጽ ፡ ፻፲ን ፡ አነጋገርና ፡ አለጥርጥር ፡ የዚሁን ፡ አንቀጽ ፡ መሠረት ፡ የሆነውን ፡ አንቀጽ ፡ ፻፳፪ን ፡ መነሻ ፡ በማድረግ ፡ በሐሳብ ፡ (በቲኦሪ) ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በግብርም ፡ (ለሕገ ፡ መንግሥቱ) ፡ በዳኝነት ፡ የተሰጠው ፡ አገላለጽ ፡ (ትርጉም) ፡ የበላይ ፡ (ሕግ) ፡ መሆን ፡ አለበት ፡ የሚለው ፡ ማጠቃለያ ፡ ሐሳብ ፡ በንጉሠ ፡ ነገ

ሥቱ ፡ እጅግ ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ ሥራ ፡ አያያዝ ፡ ምክንያት ፡ የሚነሣው ፡ ክርክር ፡ ባይኖር ፣ በሕግ ፡ አተረጓጐም ፡ ረገድ ፡ ፍጹም ፡ ቀጥታ ፡ የሆነውን ፡ መሥመር ፡ የያዘ ፡ ይመስላል ። ከዚህም ፡ በላይ ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አረቃቀቅ ፡ ታሪክ ፡ የተደገፈ ፡ ይሆናል ።

ኢትዮጵያና ፡ ኤርትራ ፡ በፌዴራሲዮን ፡ የሚዋሐዱበትን ፡ ሁናቴ ፡ ያቋቋመው የፌዴራሉ ፡ ሕግና ፡ [6] የ፲፱፻፵፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፣ በጊዜአቸው ፣ በፌዴራሉ ፡ መንግሥት ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ ሁነው ፡ ጸንተው ፡ ነበረ ። የፌዴራሉም ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በአጋጊ ፡ የታወጁ ፡ አዋጆችን ፡ ከነዚህ ፡ ሁለት ፡ ሕጎች ፡ ካንዳቸው ፡ ባለመስማማታቸው ፡ ዋጋ ፡ አልባ ፡ ለማድረግ ፡ ሥልጣን ፡ በግልጽ ፡ ተሰጥቶአቸው ፡ ነበር ። እነዚህን ፡ ሁለት ፡ መሠረታዊ ፡ ሐሳቦች ፡ የሚያቋቁሙት ፡ አንቀጾች ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ሲታዩ ፡ ለአንቀጽ ፡ ፮፳፪ ፡ ከተባበረው ፡ የአሜሪካ ፡ መንግሥት ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ "የበላይነት ፡ አንቀጽ" ፡ ይልቅ ፡ የቀረበ ፡ ምሳሌ ፡ ይሰጣሉ ።

> "የፌዴራል ፡ አዋጅና ፡ የ፲፱፻፵፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሕገ ፡ መንግሥታችን ፣ በነዚሁም ፡ መሠረት ፡ የተሠሩ ፡ የፌዴራል ፡ ሕጎች ፡ ሁሉ ፡ እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥታችን ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ ውሎች ፣ ስምምነቶችና ፡ ግዴታዎች ፡ በዚህ ፡ ትእዛዝ ፡ በኤርትራም ፡ ጭምር ፡ ሆነው ፡ በመላው ፡ በፌዴራል ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ግዛታችን ፣ ጠቅላላ ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ ይሆናሉ ።"[7]
> "....ማናቸውም ፡ ሕግ ፡ ወይም ፡ በአስተዳደር ፣ በአፈጻጸም ፣ በዳኝነት ፡ በኩል ፡ የተሰጠ ፡ ትእዛዝ ፤ ድንጋጌ ፤ ፍርድ ፤ ውሳኔ ፡ ወይም ፡ ብይን ፤ ከሕገ ፡ መንግሥታችን ፡ ወይም ፡ ከፌዴራሉ ፡ አዋጅ ፡ ጋር ፡ የሚጣላ ፡ ለመሆኑ ፡ የፌዴራል ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሕጋዊ ፡ አይደለም ፡ ብሎ ፡ የመጨረሻ ፡ ውሳኔ ፡ ሲሰጥበት ፡ የተባለው ፡ ሕግ ፤ ትእዛዝ ፤ ድንጋጌ ፤ ፍርድ ፤ ውሳኔ ፤ ወይም ፡ ብይን ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ግዛታችን ፡ ሁሉ ፡ ስርዝና ፡ ፍርስ ፡ ሆኖ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ግዛታችን ፡ ውስጥ ፡ ማንኛውም ፡ የመንግሥት ፡ ሠራተኛ ፡ ወይም ፡ ማናቸውም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አይሠራበትም ፡ ወይም ፡ እሥራ ፡ ላይ ፡ አያውለውም ።"[8]

ስለዚህ ፡ ስለ ፡ ዳኝነት ፡ የበላይነት ፡ ጥያቄውን ፡ በሌላ ፡ እነጋገር ፡ በሚከተለው ፡ ዓይነት ፡ ማቅረብ ፡ ምንም ፡ አድልኦ ፡ ያለበት ፡ አይመስልም ። ለአንቀጽ ፡ ፮፳፪ ፡ ተራ ፡ ትርጉሙ ፡ የሆነው ፣ የዳኝነት ፡ የበላይ ፡ ባለሥልጣንነት ፡ እምነት ፣ ለወደፊት ፡ መስፋፋት ፡ አቅጣጫ ፡ የሚያመለክት ፡ ብቻ ፡ ሆኖ ፡ እንዲቆጠር ፡ እስከማድረግ ፡ ድረስ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ ሥልጣን ፡ ያስፋፋልን ?

የሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ ፍች ፡ የመጨረሻው ፡ ገላጭ ፡ ሆኖ ፡ ለመሥራት ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ያለው ፡ ሥልጣን ፡ በክርክሩ ፡ ውስጥ ፡ አለመግባቱ ፡ ልብ ፡ መደረግ ፡ አለበት ። ሕጎችን ፡ ሁሉ ፡ የሚያጸድቅ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ስለሆነና ፡ ማንኛውንም ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ ይግባኝ ፡ ለመስማት ፡ ስለሚችል ፤ የበላይነቱ ፡ (የሕገ ፡

---

6 ኤን ፡ ማሬን ፡ ዘ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ኢምፓየር ፡ ፌዴሬሽን ፡ አንድ ፡ ሎው ፡ (፲፱፻፶፩ ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ) ፡ አፔንዲክስ ፡ ፩ ፤ በፌዴራል ፡ አክት ፡ ውስጥ ፡ የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያና ፡ ኤርትራ ፡ ፌዴራል ፡ አቋም ፡ በነበረው ፡ ሐሳብ ፡ ላይ ፡ ኤ ፡ እ ፡ አ ፡ ፲ ፡ ፲፪ ፡ ፶ ፡ ካሳሰበው ፡ ውሳኔ ፡ የመጀመሪያዎቹ ፡ ሰባት ፡ አንቀጾች ፡ ይገኙበታል ።

7 ኤን ፡ ማሬን ፡ እላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ መጽሐፉ ፡ ገጽ ፡ ፫፻፶፯ ፡ የኤርትራን ፡ ግዛት ፡ በፌዴሬሽን ፡ የመቀላቀልና ፡ የመጨመር ፡ ፲፱፻፵፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ፯ኛ ፡ ትእዛዝ ፡ አንቀጽ ፡ ፰ ፡ ፲፪ኛ ፡ ዓመት ፡ ቊጥር ፡ ፩ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ይመለከቷል ።

8 የኢትዮጵያ ፡ የፌዴራል ፡ ዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ አዋጅ ፡ ፲፱፻፵፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አንቀጽ ፡ ፫ ፡ (ደ) አዋጅ ፡ ፺፴ ፡ (ሀ) ፲፫ኛ ፡ ዓመት ፡ ቊጥር ፡ ፩ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ይመለከቷል ።

መንግሥቱን ፡ ፍች ፡ ለማብራራት) ፡ ለአጋጊውም ፡ ተሰጠ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቶች ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሥልጣን ፡ ረገድ ፡ ሲታይ ፡ ውጤቱ ፡ አይለወጥም ፤ (ያው ፡ ነው) ፡ ይልቁንስ ፤ ጥያቄው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ አጋጊው ፡ ያወጣውን ፡ ሕግ ፡ ቀደም ፡ ብሎ፡ ተስማምቶበት ፡ ያወጀው ፡ መሆኑና ፡ በኋላም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የበየነውን ፡ ብይን ፡ በይግባኝ ፡ ለማየት ፡ ዕድል ፡ የሚገጥመው ፡ መሆኑ ፡ የታወቀ ፡ ሲሆን ፤ አንድ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ አጋጊ ፡ ያወጀውን ፡ ሕግ ፡ መሻሩ ፡ ፍሬ ፡ ቢስ ፡ ድካም ፡ ይሆናል ፡ ወይስ ፡ አይሆንም ፡ ነው ።

በሁለት ፡ ምክንያቶች ፡ የተነሣ ፡ ለዚህ ፡ ጥያቄ ፡ መልስ ፡ የሚሰጠው ፡ በአሉታ ፡ ነው ። አንደኛ ፤ አንድ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በአጋጊው ፡ ብይን ፡ ፈንታ ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ ለመተካት ፡ የሚያስችለው ፡ አጋጣሚ ፡ አንድ ፡ አዋጅ ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ አይደለም ፡ ስለዚህም ፡ ዋጋ ፡ አልባ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ብቻ ፡ አይደለም ። የተባበረው ፡ የአሜሪካ ፡ መንግሥት ፡ የአሠራር ፡ ልምድ ፡ ፍችን ፡ የሚያመለክት ፡ ቢሆን ፡ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሥልጣን ፡ በበለጠ ፡ አዘውትሮ ፡ የሚያገለግለው ፡ አንድ ፡ አዋጅ ፡ በአንድ ፡ የተለየ ፡ አካባቢ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ሊሠራበት ፡ አይችልም ፡ ለማለት ፡ ወይም ፡ አዋጁ ፡ በእንዲህ ፡ ያለ ፡ መንገድ ፡ ሊተረጐም ፡ አይገባውም ፡ ለማለት ፡ ይሆናል ። [10] ለምሳሌ ፡ ባለጉዳዮች ፡ እከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይግባኝ ፡ ሲያስመዘግቡ ፡ የማስመዝገቢያ ፡ ዋጋ ፡ እንዲከፍሉ ፡ የሚጠይቅ ፡ አዋጅ ፡ [11] በጠቅላላው ፡ በአብዛኛዎቹ ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፡ አስፈላጊና ፡ ሊነቀፍ ፡ የማይገባው ፡ ይሆናል ። ነገር ፡ ግን ፡ የአዋጁ ፡ ዓላማ ፡ አንድ ፡ በወንጀል ፡ የተከሰሰ ፡ ደሃን ፡ የተፈረደበትን ፡ ብይን ፡ ይግባኝ ፡ ከማለት ፡ የአገደ ፡ እንደሆነ ፤ እዚህ ፡ ላይ ፡ የአዋጁ ፡ አፈጻጸም ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ በሕግ ፡ እኩል ፡ ሆኖ ፡ ለመጠበቅ ፡ ያለውን ፡ መብት ፡ [12] እንደ ፡ መንሳት ፡ ያህል ፡ ነው ፡ የሚያሰኝ ፡ ክርክር ፡ ያስነሣል ። የከፍተኛው ፡

---

9 ከሽቹኖቪች ፡ እላይ ፡ በሁለተኛው ፡ ግርጌ ፡ መግለጫ ፡ በተጠቀሰው ፡ ጽሑፍ ፡ ፻፱ ፡ ገጽ ፡ ላይ ፡ አንቀጽ ፡ ፻፳፪ ፡ በጠቅላላው ፡ ፕሮግራም ፡ አዘጋጅ ፡ ነው ፡ ተብሏል ።

10 ለማነጻጸሪያ ፡ የ፲፱፻፵፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከሰዎችና ፡ ከሥራዎች ፡ ሁሉ ፡ ግብር ፡ እንዲከፈል ፡ የሚወሰን ፡ አዋጅ ፡ አንቀጽ ፡ ፲፫—፻፶፫ኛ ፡ አዋጅ ፤ ፳ኛ ፡ ዓመት ፡ ቍጥር ፡ ፲፪ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ውስጥ ፡ ወዲያው ፡ እንዲፈጸሙ ፡ የሚለውን ፡ አነጋገር ፡ በመተርጐም ፡ የከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ነገረ ፡ ፈጅና ፡ በሳሪስ ፡ መካከል ፡ ለነበረው ፡ ክስ ፡ ስለ ፡ ሰጠው ፡ ትርጉም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ቮሉዩም ፡ ፭ ፡ ገጽ ፡ ፻፺፳ና ፡ ፻፻ ፡ ይመለከቷል ።

11 የተጠቀሰው ፡ ሕግ ፡ ለምሳሌ ፡ የቀረበ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ነው ፤ ባሁኑ ፡ አሠራር ፡ ለከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የወንጀል ፡ ይግባኝ ፡ ፋይል ፡ ለመክፈት ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አምስት ፡ ብር ፡ ይከፈላል ፡ ይህም ፡ ክፍያ ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እራሱ ፡ በአወጣው ፡ ደንብ ፡ መሠረት ፡ ነው ፤ ለፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሥርዓት ፡ አፈጻጸም ፡ በ፲፱፻፴፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የወጣ ፡ ደንብ ፡ ፴፫ኛ ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ ፺፫ኛ ፡ ክፍል ፡ ፫ኛ ፡ ዓመት ፡ ቍጥር ፡ ፪ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ይመለከቷል ።

ለድሆች ፡ የተለየ ፡ ደንብ ፡ ባይኖርም ፡ ጸሐፊው ፡ እንደተረዳው ፡ ድሆች ፡ ይህን ፡ የወንጀል ፡ ይግባኝ ፡ ፋይል ፡ መክፈቻ ፡ ዋጋ ፡ እንዳይከፍሉ ፡ መፍቀድ ፡ የተለመደ ፡ ነው ። ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ አፈጻጸም ፡ የራሱን ፡ ደንብ ፡ ማሻሻሉ ፡ በፍርድ ፡ ቤትና ፡ በሕግ ፡ አውጭው ፡ ክፍል ፡ መካከል ፡ መኖር ፡ ስለሚገባው ፡ ግንኙነት ፡ አከራካሪ ፡ ጉዳይ ፡ ሊፈጥር ፡ አይችልም ።

12 የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፴፯ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ በሕግ ፡ እኩል ፡ ሆኖ ፡ ይጠበቃል ። የተባበረው ፡ የአሜሪካ ፡ መንግሥት ፡ ጠቅላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በቀረቡለት ፡ ብዙ ፡ ክሶች ፡ ላይ ፡ በወንጀል ፡ የተከሰሱ ፡ ድሆች ፡ ለይግባኝ ፡ የሚከፈል ፡ ገንዘብ ፡ በማጣታቸው ፡ ለስ ፡ ይግባኝ ፡ የእኩልነት ፡ መብታቸውን ፡ ሲነፈጉ ፡ አይገባም ፡ የሚል ፡ ውሳኔ ፡ ተሰጥቶባቸዋል ። (ለምሳሌ ፡ ዶግለስና ፡ የካሊፎርኒያ ፡ ሕግ ፡ አስከባሪ ፡ በተከራከሩበት ፡ ክስ ፡ ጠቅላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፲፱፻፷፫ ፡ ዩናይትድ ፡ ስቴትስ ፡ ሪፖርትስ ፡ ቮሉዩም ፡ ፫፻፸፪ ፡ ገጽ ፡ ፫፻፶፫ ፡ ሎውየርስ ፡ ኤድ ፡ ፪ኛ ፡ እትም ፡ ቮሉዩም ፡ ፱ ፡ ገጽ ፡ ፰፻፲፩ ፡ ይመለከቷል) ። የነዚህም ፡ ክሶች ፡ ውሳኔዎች ፡ በዩናይትድ ፡ እስቴትስ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ስለ ፡ እኩልነት ፡ በተሰጠው ፡ መብት ፡ ላይ ፡ የተመሠረቱ ፡ ይመስላል ፡ ጠቅላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በ፲፱፻፷፪ ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ (ሐርቫርድ ፡ ሎው ፡ ሪቪው ፡ ቮሉዩም ፡ ፸፯ ፡ ፲፱፻፷፫ ፡ ገጽ ፡ ፳፪ ፡ (፻፯ ፡ ይመለከቷል) ።

ፍርድ ፡ ቤትም ፡ ይህን ፡ አስተያየት ፡ ወስዶ ፡ አዋጁ ፡ ይግባኝ ፡ በሚሉ ፡ ድሃ ፡ ወንጀለኞች ፡ ላይ ፡ ሊፈጸም ፡ አይችልም ፤ ብሎ ፡ ቢወስን ፤ አዋጁ ፡ በምንም ፡ መን ገድ ፡ ዋጋ ፡ አልባ ፡ አልተደረገም ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፴፯ ፡ ከሚሰጠው ፡ ፍች ፡ መንፈስ ፡ ጋር ፡ ለማስማማት ፡ አዋጁ ፡ እንዲሻሻል ፡ ብቻ ፡ ተደርጎአል ። አዋጁና ፡ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ብይን ፡ በሁለት ፡ የተለዩ ፡ ጠቅላላ ፡ ሁና ቴዎች ፡ ላይ ፡ የሚፈጸሙ ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ ምንም ፡ የነገር ፡ መዛባት ፡ ሳይፈጠር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ አዋጁንና ፡ አዋጁን ፡ ያሻሻለውን ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ብይን ፡ ማለት ፡ ሁለቱንም ፡ ለማጽደቅ ፡ ይችላል ።

ሁለተኛ ፤ ሕጎች ፡ ሁሉ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መፈቀድ ፡ ቢኖርባቸውም ፡ የጸ ኝነት ፡ ብይኖች ፡ ይህ ፡ ዓይነቱ ፡ ግዴታ ፡ የሚደርስባቸው ፡ አንድ ፡ ጉዳይ ፡ በን ጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ችሎት ፡ እንዲታይ ፡ አቤቱታ ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ አቤቱታውን ፡ መቀበል ፡ ወይም ፡ መንሣት ፡ አለበት ፡ በሚል ፡ ጠባብ ፡ መንፈስ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ይህ ፡ ልዩነት ፡ ስለ ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊነቱ ፡ ጥልቅ ፡ አስተያየት ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ በሐሳብ ፡ ሊለያዩበት ፡ የሚችሉበት ፡ አዋጅ ፡ ባጋጠመ ፡ ጊዜ ፡ ዋና ፡ ነገር ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። ለምሳሌ ፡ በእንዲህ ፡ ያለው ፡ ሁናቴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገ ሥቱ ፡ አዋጁን ፡ ቢፈቅድ ፡ ማለት ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ቢወስን ፡ በኋላ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ አይደለም ፡ የሚያሰኝ ፡ ውሳኔ ፡ ላይ ፡ ደርሶ ፡ አዋጁ ፡ ዋጋ ፡ አልባ ፡ ነው ፡ ሲል ፡ ቢበይንና ፡ የተረታው ፡ ወገን ፡ ጉዳዩ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ችሎት ፡ እንዲታይለት ፡ አቤት ፡ ቢል ፤ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ቀደም ብሎ ፡ አዋጁ ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ ነው ፡ ብሏልና ፡ አቤቱታውን ፡ ፈቅዶ ፡ ፍር ዱን ፡ መገልበጥ ፡ አለበት ፡ ማለት ፡ ነውን? ወይስ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች የሕግን ፡ ፍች ፡ የመግለጽ ፡ ወይም ፡ የማብራራት ፡ ኀላፊነታቸውን ፡ በሚፈጽሙ በት ፡ ጊዜ ፡ የራሳቸውን ፡ አስተያየት ፡ እንዲያደርጉ ፡ ቢፈቀድላቸው ፡ የሕገ ፡ መን ግሥቱ ፡ ዓላማ ፡ በበለጠ ፡ ይፈጸማል ፡ በማለት ፡ አቤቱታውን ፡ መቀበል ፡ አይገ ባም ፡ ብሎ ፡ ይወስን ፡ ይሆን? ከሁለቱ ፡ የኋለኛው ፡ መንገድ ፡ መመረጡ ፡ የተረጋ ገጠ ፡ አይደለም ። ይሁን ፡ እንጂ ፤ ፍርድ ፡ ቤቶቹ ፡ በአንቀጽ ፡ ፻፲ና ፡ ፻፳፪ ፡ የተጣ ለባቸው ፡ የሚመስለውን ፡ ኀላፊነት ፡ አስቀድሞ ፡ ካልተቀበሉ ፡ እንዲያውም ፡ ምርጫው ፡ አይኖርም ።

ከተሸሹት ፡ ጥያቄዎች ፡ ሁለተኛው ፡ የአንቀጽ ፡ ፻፳፪ ፡ "ወደፊት ፡ በሚሠሩ ፡ ሕጎች ፡ ድንጋጌዎች ፡ ፍርዶች ፡ ውሳኔዎች" ፡ ("ወደፊት" ፡ በሚለው ፡ ቃል ፡ ሥር ለአጋኖ ፡ ሲባል ፡ መሥመር ፡ አድርገናል) ፡ መወሰን ፡ የሚያቀርበው ፡ ጥያቄ ፡ ነው። በአንቀጽ ፡ ፻፳፪ ፡ አነጋገር ፡ የአስተዳደር ፡ ተግባሮች ፡ (በቃሉ ፡ ሕጎችን ፡ ድንጋጌ ዎችንና ፡ ሌሎችንም ፡ ለማጠቃለያ ፡ በመገልገል) ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ከታወጀ በት ፡ ከጥቅምት ፡ ፳፬ ፡ ቀን ፡ በፊት ፡ በተፈጸሙና ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ከታወጀ ፡ ወዲህ ፡ በተፈጸሙ ፤ ሁለት ፡ ክፍሎች ፡ ተከፍለዋል ። ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ በሆነ ፡

---

13 ልዩነቱ ፡ ጉልህ ፡ የሚሆነው ፡ የግርማዊነታቸው ፡ ችሎት ፡ እንደ ፡ መጨረሻ ፡ የይግባኝ ፡ ችሎት ፡ ሳይሆን ፡ ልዩ ፡ ንጉሣዊ ፡ ሥልጣንና ፡ መብት ፡ የሚገለጽበት ፡ አቋም ፡ ነው ፤ ሲባል ፡ ነው ። አር ፡ ሴድለር ፡ "ዘ ፡ ችሎት ፡ ጁሪሲዲክሽን ፡ ኦፍ ፡ ዘ ፡ ኢምፓየር ፡ ኦፍ ፡ ኢትዮጵያ" ፤ ጆርናል ፡ ኦፍ ፡ አፍሪካን ፡ ሎው ፡ ቮሉዩም ፡ ፰ ፡ ፲፱፻፷፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ ገጽ ፡ ፺፱ ፡ ፹፯ና ፡ ተከታዩን ፡ ይመለ ከቷል ። ችሎት ፡ እንደ ፡ መጨረሻ ፡ የይግባኝ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ቢወሰድም ፡ እንኳ ፡ ማንኛውንም ፡ ክስ ፡ ለመመርመር ፡ ሆነ ፡ ላለመመርመር ፡ ወሰን ፡ የሌለው ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ሲሆን ፡ ክሱን ፡ እንመረምርም ፡ የሚል ፡ የአስተያየት ፡ ውሳኔ ፡ በሚሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ በበታች ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የተሰ ጠውን ፡ ውሳኔ ፡ እንደማጽደቅ ፡ ሊቆጠር ፡ አይገባም ። ኤ ፡ ቢኬል ፡ ፎርወርድ ፡ ዘ ፡ ፖሲቲቭ ፡ ቨርቹስ ፡ ሐርቨርድ ፡ ሎው ፡ ሪቪው ፡ ቮሉዩም ፡ ፸፭/፲፱፻፷፩ ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ ገጽ ፡ ፵ ፡ ይመለከቷል ።

ምክንያት ፣ ዋጋ ፣ የሌላቸውና ፣ የማያገለግሉ ፣ ይሆናሉ ፣ የተባሉት ፣ የኋለኞቹ ፣ ብቻ ፣ ናቸው ።

ሕገ ፣ መንግሥታዊ ፣ በሆነ ፣ ምክንያት ፣ የሌሎች ፣ የመንግሥት ፣ ቅርንጫፎች ፣ ተግባሮችን ፣ ለመሻር ፣ የፍርድ ፣ ቤቶች ፣ የሥልጣን ፣ መሠረት ፣ አንቀጽ ፣ ፻፰ ፣ ብቻ ፣ ነው ፣ የሚባል ፣ ቢሆን ፤[14] በፍርድ ፣ ቤቶች ፣ ሥልጣን ፣ ሥር ፣ የሚወድቁት ፣ ከጥቅምት ፣ ፳፬ ፣ ቀን ፣ ፲፱፻፵፰ ፣ ዓ ፣ ም ፣ ወዲህ ፣ የተፈጸሙ ፣ ተግባሮች ፣ ብቻ ፣ ናቸው ።[15] በፍርድ ፣ ቤት ፣ እንደገና ፣ መታየትን ፣ አጥብቀው ፣ ለሚደግፉ ፣ ወገኖች ፣ እንኳን ፣ ይህ ፣ ግልጽ ፣ ነው ። ግልጽ ፣ ያልሆነው ፣ ግን ፣ (በተለይም ፣ ለነዚህ ፣ ደጋፊዎች) ፣ ሁለት ፣ ያስተዳደር ፣ ተግባሮች ፣ አንዱ ፣ ሕገ ፣ መንግሥቱ ፣ ከመታወጁ ፣ በፊት ፣ ሌላው ፣ ሕገ ፣ መንግሥቱ ፣ ከታወጀ ፣ በኋላ ፣ የተፈጸሙ ፣ ሆነው ፣ አንድ ፣ ላይ ፣ መታየት ፣ በሚገባቸው ፣ ጊዜ ፣ የዚህ ፣ ወሰን ፣ ተገቢ ፣ አፈጻጸም ፣ እንዴት ፣ እንደሆነ ፣ ነው ። ለምሳሌ ፣ የሚከተሉትን ፣ ልብ ፣ ወለድ ፣ ጉዳዮች ፣ እንመልከት ፡—

<u>፩ኛ ፣ ጉዳይ</u> ፤ አንድ ፣ የመንግሥት ፣ መሥሪያ ፣ ቤት ፣ በ፲፱፻፵፫ ፣ ዓ ፣ ም ፣ የታወጀ ፣ አዋጅ ፣ በሚያዘው ፣ መሠረት ፣ የ"ፐ"ን ፣ ቦታ ፣ ምንም ፣ ግምት ፣ ሳይከፈለው ፣ እንዲወስድ ፣ በ፲፱፻፶፯ ፣ ዓ ፣ ም ፣ ያዝዛል ። "ፐ" ፣ የቦታው ፣ መወሰድ ፣ በሕገ ፣ መንግሥት ፣ አንቀጽ ፣ ፵፫ና ፣ ፵፩ ፣ መሠረት ፣ ሕገ ፣ መንግሥታዊ ፣ አይደለም ፣ ብሎ ፣ ይከራከራል ።[16]

<u>፪ኛ ፣ ጉዳይ</u> ፤ በ፲፱፻፶፯ ፣ ዓ ፣ ም ፣ የአዲስ ፣ አበባ ፣ ማዘጋጃ ፣ ቤት ፣ ምክር ፣ ቤት ፣ "ፐ" ፣ እንዲከፍል ፣ የተገመተበትን ፣ ቀረጥ ፣ ያጸድቃል ። ጉዳዩ ፣ በምክር ፣ ቤቱ ፣ በሚታይበትም ፣ ጊዜ ፣ ሆነ ፣ ወይም ፣ ቀደም ፣ ብሎ ፣ "ፐ" ፣ ለተገመተበት ፣ ግምት ፣ መቃወሚያ ፣ ማስረጃ ፣ እንዲያቀርብ ፣ ወይም ፣ እንዲከራከር ፣ ዕድል ፣ አልተሰጠውም ። "ፐ" ፣ ይህ ፣ ንብረቱን ፣ ያለሕግ ፣ (ያለተገቢ ፣ ሕጋዊ ፣ ሥነ ፣ ሥርዓት) ፣ እንደማጣት ፣ የሚቆጠር ፣ ነው ፣ ይላል ። በ፲፱፻፵፫ ፣ ዓ ፣ ም ፣ አዋጅ ፣ አነጋገር ፣ የማዘጋጃ ፣ ቤቱ ፣ ምክር ፣ ቤት ፣ ውሳኔዎች ፣ የመጨረሻና ፣ በፍርድ ፣ ቤት ፣ እንደገና ፣ የማይታዩ ፣ ናቸው ።[17]

---

14 የተባበረው ፣ የአሜሪካ ፣ መንግሥትን ፣ ምሳሌነት ፣ በመውሰድ ፣ ተቃራኒ ፣ ክርክር ፣ ለማቅረብ ፣ ይቻላል ፤ ከዚህ ፣ በላይ ፣ ፩ኛውን ፣ ቍጥር ፣ የግርጌ ፣ ማስረጃ ፣ ይመለከቷል ።

የኢትዮጵያ ፣ ፍርድ ፣ ቤቶች ፣ በአንቀጽ ፣ ፻፰ ፣ ሳይጠቀሙ ፣ አጋጊ ፣ ያወጣቸውን ፣ ሕጎች ፣ ውድቅ ፣ የማድረግ ፣ ሥልጣን ፣ አላቸው ፣ ቢባልም ፣ እንኳ ፣ ይህ ፣ አንቀጽ ፣ በሕገ ፣ መንግሥቱ ፣ ውስጥ ፣ እንደ ፣ መገኘቱ ፣ መጠን ፣ ሥልጣናቸው ፣ በአንቀጹ ፣ አነጋገር ፣ የተወሰነ ፣ ነው ፣ የሚለው ፣ አስተያየት ፣ የተሻለ ፣ መስሎ ፣ ይታያል ።

15 በልጅ ፣ እርአያ ፣ አበበና ፣ በኢትዮጵያ ፣ ን ፣ ነ ፣ መ ፣ የቴሌኮሙኒኬሽን ፣ ቦርድ ፣ መካከል ፣ በከፍተኛው ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ፲፱፻፶፭ ፣ የነበረው ፣ ክርክር ፣ የኢትዮጵያ ፣ ሕግ ፣ መጽሔት ፣ ቮሉዩም ፣ ፪ ፣ ገጽ ፣ ፫፻ ፣ ይመለከቷል ።

16 ይህ ፣ ልብ ፣ ወለድ ፣ ክስ ፣ ከፍ ፣ ብሎ ፣ በተገለጸው ፣ በ፲፭ኛው ፣ ተራ ፣ ቍጥር ፣ የግርጌ ፣ ማስረጃ ፣ በተጠቀሰው ፣ ክስ ፣ ላይ ፣ የተመሠረተ ፣ ነው ።

17 የ፲፱፻፴፯ ፣ ዓ ፣ ም ፣ የማዘጋጃ ፣ ቤት ፣ አዋጅ ፣ ቍጥር ፣ ፳፬/፲፩ኛ ፣ አንቀጽ ፣ በ፬ኛው ፣ ዓመት ፣ ቍጥር ፣ ፯ ፣ ነጋሪት ፣ ጋዜጣ ፣ ታትሞ ፣ የወጣውን ፣ መሠረት ፣ በማድረግ ፣ በ፲፱፻፵ ፣ ዓ ፣ ም ፣ የወጣ ፣ የማዘጋጃ ፣ ቤት ፣ የውሃ ፣ ዋጋ ፤ የንግድ ፣ ፈቃድ ፤ ግብርና ፣ የቀረጥ ፣ ደንብ ፣ አንቀጽ ፣ ፭ ፣ የሕግ ፣ ክፍል ፣ ማስታወቂያ ፣ ቍጥር ፣ ፻፲፯ ፣ ፯ኛ ፣ ዓመት ፣ ቍጥር ፣ ፭ ፣ ነጋሪት ፣ ጋዜጣ ፣ መሠረት ፣ ለማዘጋጃ ፣ ቤት ፣ ስለሚከፈለው ፣ ዋጋ ፣ ግምት ፣ የሚሰጠው ፣ ውሳኔ ፣ ይግባኝ ፣ የሌለው ፣ የመጨረሻ ፣ ውሳኔ ፣ መስሎ ፣ ይታያል ፣ ይህ ፣ ሕግም ፣ ታትመው ፣ በወጡ ፣ ሁለት ፣ ክሶች ፣ ውስጥ ፣ ገብቶ ፣ ተጠቅሷል ።

(ይግባኝ ፣ የመስማት ፣ ሥልጣን ፣ ይቀበላል) ፣

(ይግባኝ ፣ የመስማት ፣ ሥልጣን ፣ አይቀበልም) (ተመሳሳይ) ።

፫ኛ ፡ ጉዳይ ፤ የ፲፱፻፶፫ ፡ የሥራ ፡ ግብር ፡ አዋጅ ፡ የአገር ፡ ውስጥ ፡ ገቢ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የገመተውን ፡ ግብር ፡ በታክስ ፡ ይግባኝ ፡ ኮሚሲዮን ፡ ወይም ፡ በፍርድ ፡ ቤቶች ፡ እንዳይታይ ፡ ለማድረግ ፡ በ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ታርሟል ። ይህ ፡ ከሆነ ፡ በኋላ ፡ "ጥ" ፡ የተገመተበትን ፡ የሥራ ፡ ግብር ፡ በ፪ኛው ፡ ጉዳይ ፡ በተመለከተው ፡ ምክንያት ፡ ለመቃወም ፡ ይሞክራል ።

፫ኛው ፡ ጉዳይ ፡ የተጨመረው ፡ የማያጠራጥረውን ፡ ለማመልከት ፡ ያህል ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ በ፫ኛው ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ አሻሚ ፡ ሁኔታዎች ፡ ቢኖሩ ፤ አንቀጽ ፡ ፻፳፪ ፡ ወደፊት ፡ በሚደረጉ ፡ ያስተዳደር ፡ ተግባሮች ፡ ብቻ ፡ በመወሰኑ ፡ የተፈጠሩ ፡ አይደሉም ። በክርክር ፡ ሊገቡ ፡ የሚችሉት ፡ ሁለቱም ፡ ተግባሮች ፡ ማለት ፡ የአዋጅ ፡ መታረምና ፡ አለአግባብ ፡ ተደረገ ፡ የተባለው ፡ ግምት ፡ የተፈጸሙት ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ከታወጀ ፡ በኋላ ፡ ነው ።

የፍርድ ፡ ቤቱን ፡ ኀላፊነት ፡ በአንድ ፡ በኩል ፡ ስንመለከተው ፡ የመጀመሪያ ዎቹ ፡ ሁለት ፡ ጉዳዮች ፡ ፍርድ ፡ ቤቱን ፡ መላ ፡ የሚያሳጡ ፡ ናቸው ። በ፩ኛው ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ የተፈጸመውን ፡ የንብረት ፡ መወሰድ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ነው ፡ ያለ ፡ እንደሆነ ፤ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ከመታወጁ ፡ በፊት ፡ የታወጀውን ፡ ሕግ ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ በሆነ ፡ ምክንያት ፡ መሻሩ ፡ ይሆናል ። በ፪ኛውም ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ነገሩን ፡ ለመስማት ፡ ሥልጣን ፡ የወሰደ ፡ እንደሆነ ፡ እንኳን ፡ ይህንኑ ፡ አደ ረገ ፡ ማለት ፡ ነው ። በምንም ፡ ዓይነት ፡ አነጋገር ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ቢጠቀም ፡ በየ አንዳንዱ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ የሚሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ የሚያመለክተው ፡ የቀረቡለትን ፡ ጉዳዮች ፡ በመሰሉ ፡ ነገሮች ፡ ረገድ ፡ የ፲፱፻፷፫ን ፡ አዋጅ ፡ ውጤት ፡ እንደማይሰጥ ፤ ዋጋ ፡ እንደሌለውና ፡ እንደማያገለግል ፤ አድርጎ ፡ ቆጥሮታል ፡ ማለት ፡ ነው ። በ፩ኛው ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ የመንግሥት ፡ ወኪሎች ፡ የ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ ፡ ምን ፡ አዋጅ ፡ መመሪያ ፡ እንዲከተሉ ፡ ካልተፈቀደላቸው ፡ ወይም ፡ የ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አዋጅ ፡ በ፪ኛው ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ የጉዳዩን ፡ እንደገና ፡ መታየት ፡ የማያግድ ፡ ከሆነ ፤ አዋጆቹ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ መዋላቸው ፡ ቀርቷል ፡ ማለት ፡ ነው ። የተገለበ ጠው ፡ የ፲፱፻፶፯ቱ ፡ ተግባር ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አዋጅ ፡ አይ ደለም ፡ ማለትም ፡ ቃል ፡ ማሳመር ፡ ብቻ ፡ ይሆናል ።

በዚህ ፡ ፈንታ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የዚህ ፡ ተቃራኒ ፡ መንገድ ፡ ቢከተልና ፡ በኋላ ፡ (ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ከታወጀ ፡ ወዲህ) ፡ ከተፈጸሙት ፡ ተግባሮች ፡ ይልቅ ፡ የቀድሞ ዎቹ ፡ (ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ከመታወጁ ፡ በፊት) ፡ አዋጆች ፡ የታወጁበትን ፡ ቀን ፡ ቢመለከት ፡ የሚገኘው ፡ ውጤት ፡ የ"ጥ"ን ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ የሆነ ፡ መብት ፡ የጣሰ ፡ ከ፲፱፻፷፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ወዲህ ፡ የተፈጸመን ፡ የመንግሥት ፡ የአስተዳደር ፡ ተግ ባር ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ከመታየት ፡ እንዲድን ፡ ማድረግ ፡ ይሆናል ። "ጥ" ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ የተሰጠው ፡ መብት ፡ ተጠብቆለታል ፡ የሚለው ፡ የአንድ ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ የማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ውሳኔ ፡ መብቱ ፡ አልተጠበቀለትም ፡ ከሚለው ፡ ከፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ብይን ፡ ያላነሰ ፡ ሥልጣን ፡ እንዳለው ፡ የሚቆጠር ፡ ከሆነ ፡ ይህ ፡ ውጤት ፡ የሚነቀፍበት ፡ ነገር ፡ የለም ። አንቀጽ ፡ ፻፲ና ፡ አንቀጽ ፡ ፻፳፪ ፡ የሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ ፍች ፡ በመግለጽ ፡ ረገድ ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የበላይ ፡ ባለሥልጣን ፡ መሆናቸውን ፡ የሚያመለክቱ ፡ ሆነው ፡ ሊወሰዱ ፡ ይገባል ፡ ተብሎ ፡ እንደቀረበው ፡ ክርክር ፡ ከተወሰዱ ፡ አንቀጽ ፡

፪፻፪ን ፡ አሚልቶ ፡ መጠበቅ ፡ ወይም ፡ አለመጠበቅ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ከተተወው፡ ምርጫ ፡ ውስጥ ፡ አይገኝም ። [18]

ከፍ ፡ ብሎ ፡ በተደረገው ፡ አቀራረብ ፡ ሲገለጽ ፡ ያው ፡ ችግር ፡ በያንዳንዱ ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ ይደቀናል ። ይሁን ፡ እንጂ ፤ ችግሮቹ ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ አይደሉም ፤ መፍትሔአቸውም ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ መሆን ፡ አለበት ፡ አይባልም ።

በ፪ኛው ፡ ጉዳይ ፡ እንጀምር ። በዚያ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ከችግሩ ፡ መውጫ ፡ የሚሆነው ፡ አንድ ፡ መንገድ ፡ የመንግሥትን ፡ የአስተዳደር ፡ ተግባር ፡ ዋጋ ፡ የሌለውና፡ የማያገለግል ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ አንድ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ሥልጣን ፡ የሚኖረው ፤ ተግባሩ ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ሊሆን ፡ ይገባል ፡ የሚል ፡ ክስ ፡ በሥርዓት ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የቀረበ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ፤ በሚለው ፡ መሠረተ ፡ ሐሳብ ፡ በመጠቀም ፡ ነው ። ምናልባትም ፡ መምራት ፡ የሚገባው ፡ ይህ ፡ (የክስ ፡ መቅረብ ፡ ማስፈለግ) ፡ መሠረተ ፡ ሐሳብ ፡ ይሆናል ። ይሁን ፡ እንጂ ፤ ከአንቀጽ ፡ ፪፻፪ ፡ ዓላማ ፡ ጋር ፡ በተሻለ ፡ የሚስማማ ፡ ሌላ ፡ የአመራመር ፡ መንገድ ፡ ደግሞ ፡ አለ ።

የዚህ ፡ የኋለኛው ፡ የአመራር ፡ መንገድ ፡ መሠረት ፡ በ፪ኛው ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ ክርክር ፡ በተነሳባቸው ፡ በሁለቱ ፡ የመንግሥት ፡ ተግባሮች ፡ ጠባይ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ጥልቅ ፡ ልዩነት ፡ ነው ። ማስረጃ ፡ ለማቅረብ ፡ ወይም ፡ ለመከራከር ፡ የማዘጋጃ ፡ ቤቱ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ለ“ፐ” ፡ ፈቃድ ፡ መከልከሉ ፤ የዳኝነት ፡ ብይን ፡ የሚያስፈልገው ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ የሆነ ፡ ክርክር ፡ ያስነሣል ። ፍርድ ፡ ቤትም ፡ ጉዳዩን ፡ ለመስማት ፡ ከወሰነ ፡ የሚሰጠው ፡ ብይን ፡ የማዘጋጃ ፡ ቤቱ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ወደፊት ፡ ሊከተል ፡ የሚገባውን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ይወስን ፡ ይሆናል ። የጉዳዩን ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ እንደገና ፡ መታየት ፡ ስለሚያግደው ፡ አዋጅ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሚሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ ግን ፡ ማለት ፡ ጉዳዩን ፡ ለመስማት ፡ ሥልጣን ፡ በመውሰድ ፡ ረገድ ፡ የሚሰጠው ፡ ውሳኔ ፡ በራሱ ፡ ስለ ፡ አለፈው ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ወደፊቱ ፡ የምክር ፡ ቤቱ ፡ ተግባሮች ፡ ምንም ፡ አይወስንም ። የተባለው ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔ ፡ የሚያረጋግጠው ፡ በማዘጋጃ ፡ ቤቱ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ውሳኔ ፡ ላይ ፡ የመጨረሻ ፡ ቃል ፡ የሚኖረው ፡ የትኛው ፡ ድርጅት ፡ (ፍርድ ፡ ቤት ፡ ወይስ ፡ የማዘጋጃ ፡ ቤቱ ፡ ምክር ፡ ቤት) ፡ መሆኑን ፡ ነው ። ማለት ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሁለቱ ፡ ክርክሮች ፡ ሕግን ፡ ከሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በሚለየው ፡ መሥመር ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ የሚውሉ ፡ ናቸው ። [19]

---

18 ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ለመተርጐም ፡ የበላይነት ፡ ሥልጣን ፡ ቢሰጣቸው ፡ አዋኪ ፡ ሁኔታ ፡ ለመፍጠር ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ አይሆንም ፡ ብሎ ፡ በመጠኑ ፡ ለመከራከር ፡ ይቻላል ። በዚህ ፡ ረገድ ፡ የፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የበላይነት ፡ ሊኖር ፡ የሚችለው ፡ የትርጉሙ ፡ ክርክር ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ ሲቀርብ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ግልጽ ፡ ድንጋጌ ፡ አለመኖሩ ፡ እየታወቀ ፡ አንድ ፡ የአስተዳደር ፡ አድራጎት ፡ ወይም ፡ አጋጊ ፡ ያወጣው ፡ ሕግ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲታይ ፡ ለመጠየቅ ፡ በሕገ ፡ መንግሥት ፡ የተጠበቀ ፡ መብት ፡ አለ ፡ ብሎ ፡ ያለአንዳች ፡ ምርምር ፡ መቀበል ፤ በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ መጀመሪያ ፡ ላይ ፡ ለቀረበው ፡ ጥያቄ ፡ በይሆናል ፡ የግምት ፡ መልስ ፡ ከመስጠት ፡ ይቆጠራል ። ለዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ መቃወሚያ ፡ ግምቱን ፡ አምነን ፡ ብንቀበል ፡ ከትክክለኛ ፡ አስተሳሰብ ፡ ውጭ ፡ ያልሆነ ፡ ክርክር ፡ ሊመሠረትበት ፡ ይቻላል ፡ የሚል ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ ይቻላል ፤ አንድ ፡ የአስተዳደር ፡ አድራጎት ፡ ወይም ፡ አጋጊ ፡ ያወጣው ፡ ሕግ ፡ በፍርድ ፡ ቤቶች ፡ እንዲታይ ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ መብት ፡ የሚሰጥ ፡ ከሆነ ፡ የተወሰደው ፡ ግምት ፡ ትክክለኛ ፡ ሆነ ፡ ማለት ፡ ነው ። ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ መብቱን ፡ የማይሰጥ ፡ ከሆነ ፡ ደግሞ ፡ ለዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ዓላማ ፡ በክርክሩ ፡ አወሳሰን ፡ ላይ ፡ ለውጥ ፡ አያመጣም ።

19 ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የመሠረታዊ ፡ ሕግ ፡ ጥያቄ ፡ ሆኖ ፡ የሚቀርበው ፡ ክርክር ፡ ለማዘጋጃ ፡ ቤቱ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ግን ፡ የሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ጥያቄ ፡ ነው ። ላሁኑ ፡ ምርምራችን ፡ አግባብ ፡ ያለው ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሚቀርበው ፡ መሠረታዊ ፡ የሕግ ፡ ጥያቄ ፡ ነው ።

የዚህ ፡ ልዩነት ፡ ዋና ፡ ነገር ፡ መሆን ፡ ከአንቀጽ ፡ ፻፳፪ ፡ ሁለት ፡ ዓላማዎች ፡ ያፈልቃል ። ከአንቀጹ ፡ ዓላማዎች ፡ አንዱ ፡ የሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ በተለይም ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ለሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ የሚሰጡትን ፡ ፍች ፡ የበላይነት ፡ ለማረጋገጥ ፡ መሆኑ ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ በተደረገው ፡ ክርክር ፡ ተገልጧል ። የአንቀጹ ፡ ወደፊት ፡ በሚፈጸሙ ፡ የመንግሥት ፡ ተግባሮች ፡ ብቻ ፡ መገታት ፡ ግልጽ ፡ ዓላማ ፡ ግን ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ማገጃዎች ፡ ወደኋላ ፡ መመልከት ፡ ምክንያት ፡ የሚነሱትን ፡ ችግሮች ፡ ለማስወገድ ፡ ነው ።

እንደ ፡ ኋለኛው ፡ ባለ ፡ ዓላማ ፡ ረገድ ፡ በሕግና ፡ በሥነ ፡ ሥርዓት ፡ መካከል ፡ አንድ ፡ ዋና ፡ ልዩነት ፡ አለ ። ለምሳሌ ፡ አንድ ፡ ተዋዋይ ፡ ውሉ ፡ ከመፈጸሙ ፡ በፊት ፡ ውል ፡ የሚፈጸምበትን ፡ ሁናቴ ፡ የሚወስነው ፡ ሕግ ፡ ቢለወጥበት ፡ እንደ ፡ ተጭበረበረ ፡ አድርጎ ፡ በሚገባ ፡ ሊቆጥረው ፡ ይችል ፡ ይሆናል ። (የባለውሉ ፡ ቅሬታ ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ ደረጃ ፡ ማግኘት ፡ አለማግኘቱ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ ነው) ። በሕጉ ፡ ላይ ፡ ከውሉ ፡ የሚነሱ ፡ ክሶች ፡ በፊት ፡ በሚታዩበት ፡ ቀርቶ ፡ በሌላ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይታያሉ ፡ የሚል ፡ ለውጥ ፡ ቢደረግ ፡ ግን ፡ በጠቅላላው ፡ ባለውሉ ፡ በነበረው ፡ ጽኑ ፡ ተስፋ ፡ ላይ ፡ የሚደርስ ፡ ከባድ ፡ ጉዳት ፡ አይኖርም ። ወይም ፡ በሌላ፡ ምሳሌ፡ለመጠቀም ፡ የ፲፱፻፵፫ ፡ ዓ፡ ም፡ የሥራ፡ ግብር፡ አዋጅ ፡ ከ፲፱፻፵፫ ፡ ዓ፡ ም፡ በፊት ፡ ያሉትን ፡ ዓመታት ፡ የግብር ፡ ዕዳ ፡ አለወጠም ። ይህን ፡ ቢያደርግ ፡ ኖሮ፡ ብዙዎች ፡ ሰዎች ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ በደል ፡ አድርገው ፡ ይቆጥሩት ፡ ነበረ ። ነገር ፡ ግን ፡ በነዚያ ፡ ባለፉት ፡ ዓመታት ፡ የግብሩ ፡ አከፋፈል ፡ የተወሰነበትን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በ፲፱፻፵፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሕግ ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ በማድረግ ፡ አንዳችም ፡ በደል ፡ አልተፈጸመ ።[20]

የአንቀጽ ፡ ፻፳፪ ፡ ወደፊት ፡ በሚሠሩ ፡ የመንግሥት ፡ ተግባሮች ፡ መወሰን ፡ እንዲያስወግዳቸው ፡ የተፈለጉት ፡ ችግሮች ፡ አንድ ፡ አዲስ ፡ የግብር ፡ ሕግ ፡ ወይም፡ አንድ ፡ አዲስ ፡ የውል ፡ ግዴታዎች ፡ ሕግ ፡ ከሚያስነሳቸው ፡ ችግሮች ፡ በዓይነት ፡ አይለዩም ። በየአንዳንዱ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ የችግሮች ፡ ምንጭ ፡ የሆነው ፡ ሰዎች ፡ (የግል ፡ ነዋሪዎች ፡ ወይም ፡ የመንግሥት ፡ ባለሥልጣኖች) ፡ በአሮጌው ፡ ሕግ ፡ በመመካት ፡ እርምጃ ፡ መውሰዳቸውና ፡ ፕላን ፡ ማድረጋቸው ፡ ነው ። አዲሱም ፡ ሕግ ፡ በየአንዳንዱ ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ተመልሶ ፡ እንዳይሠራበት ፡ መታገዱ ፡ የሰዎቹ ፡ ጽኑ ፡ አለኝታዎች ፡ ሊጠበቁ ፡ የሚገባቸው ፡ ናቸው ፡ ተብሎ ፡ ስለ ፡ ተቆጠረ ፡ ነው ። የሕግን ፡ ጉዳይ ፡ ከሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ጉዳይ ፡ ለመለየት ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ በጠቅላላ ፡ አነጋገር ፡ እነዚህን ፡ አለኝታዎች ፡ የሚያሰጋቸው ፡ በሕጉ ፡ ላይ ፡ የሚደረገው ፡ ለውጥ ፡ ብቻ ፡ ስለሆነ ፡ ነው ።

በሁለተኛው ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ በሚነጋገርበት ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ እንዲከተል ፡ ቢጠየቅ ፡ የማዘጋጃ ፡ ቤቱን ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ሊያሳስበው ፡ የሚገባ ፡ ነው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ቢያንስ ፡ ቢያንስ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓቱ ፡ ከ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በፊት ፡ በነበረ ፡ የመንግሥት ፡ ደንብ ፡ የተወሰነ ፡ ባልሆነበት ፡ ጊዜ ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ከሚወስነው ፡ ማናቸውም ፡ ደረጃ ፡ ጋር ፡ ተስማሚ ፡ የሆነ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ እንዲከተል ፡ በአንቀጽ ፡ ፻፳፪ ፡ ታዝዋል ። በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ በተቀበልነው ፡ የአንቀጽ ፡ ፻፲ና ፡ ፻፳፪ ፡ ፍችም ፡ እነዚህን ፡ ደረጃዎች ፡ የመወሰንና ፡

---

20 ማርፕለስ ፡ ሪጂዌይና ፡ ሸሪኮቹ ፡ ካገር ፡ ውስጥ ፡ ገቢ ፡ ዋና ፡ መ/ቤት ፡ ነገረ ፡ ፈጅ ፡ ጋር ፡ በተከራከሩበት ፡ (ከፍተኛው ፡ ፍ/ቤት ፡ ፲፱፻፶፮ ፡ ዓ ፡ ም) ፡ ጉዳይ ፡ የኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ መጽሔት ፡ ቮሉዩም ፡ ፩ ፡ ገጽ ፡ ፫፻፶፯ ፡ ይመለከቷል ።

እንዲሠራባቸውም ፡ የማድረጉ ፡ ተቀዳሚ ፡ ኃላፊነት ፡ የፍርድ ፡ ቤቶቹ ፡ ነው ። የ፲፱፻፹፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አዋጅ ፡ ይህን ፡ ኀላፊነት ፡ ከፍርድ ፡ ቤቶች ፡ የሚነፍግ ፡ ይመስላል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ የአስተዳደር ፡ ተግባሮችን ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ እንደገና ፡ ከመታየት ፡ የሚያግድ ፡ አዋጅ ፡ የአንቀጽ ፡ ፸፰ን ፡ ዓላማ ፡ (የአንቀጹን ፡ አነጋገር ፡ ወ/ቋንቋ ፡ ሳይሆን) ፡ የሚመለከተው ፤ ሁለተኛውን ፡ ጉዳይ ፡ በሚነካ ፡ መንገድ ፡ ከ፲፱፻፹፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በፊት ፡ የማዘጋጃ ፡ ቤቱ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ የወሰነው ፡ ጉዳይ ፡ እንደገና ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከመታየት ፡ ባለው ፡ ነጻነት ፡ ተመክቶ ፡ ነበር ፡ ያልን ፡ እንደሆነ ፡ ብቻ ፡ ነው ። እዚህ ፡ ትምክህት ፡ ላይ ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ ለመገመት ፡ ግን ፡ ቀላል ፡ አይደለም ። ከዚህ ፡ ጥቂት ፡ ለየት ፡ ባለ ፡ ሁኔታ ፡ የማዘጋጃ ፡ ቤቱ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ለራሱ ፡ ሥራ ፡ ማካሄጃ ፡ ሲል ፡ በጊዜው ፡ “ፐ”ን ፡ ማስረጃ ፡ ከማቅረብ ፡ ወይም ፡ ከመከራከር ፡ የከለከለ ፡ የሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ደንብ ፡ ሲያረቅቅ ፡ እርግጥ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ከመዳኘት ፡ በነበረው ፡ ነጻነት ፡ ተመክቶ ፡ ይሆናል ። ነገር ፡ ግን ፡ እነዚህ ፡ ደንቦች ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ከመታወጁ ፡ በፊት ፡ ተደንግገው ፡ እንደሆነ ፡ (የማዘጋጃ ፡ ቤቱም ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ትምክህት ፡ የአንቀጽ ፡ ፸፰ን ፡ ዓላማ ፡ የሚመለከተው ፡ ይህ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው) ፡ ሁለተኛው ፡ ጉዳይ ፡ እንደ ፡ አንደኛው ፡ ይሆናል ።

ከ፲፱፻፹፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በፊት ፡ የነበሩትን ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ሥልጣን ፡ መግቻዎች ፡ ችላ ፡ በማለት ፡ ባንዳንድ ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፡ ጸንተው ፡ በሚገኙት ፡ አለኝታዎች ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ፈጽሞ ፡ ሊደርስ ፡ አይችልም ፡ ለማለት ፡ ያስቸግራል ። ነገር ፡ ግን ፡ የዚህ ፡ መሳይ ፡ ጉዳት ፡ መድረስ ፡ በጣም ፡ አነስተኛ ፡ ሆኖ ፡ ስለሚታይ ፡ የሕግና ፡ የሥነ ፡ ሥርዓትን ፡ ልዩነት ፡ መሣሪያ ፡ ማድረግ ፡ እንደ ፡ ፪ኛው ፡ ባለጉዳይ ፡ ላይ ፡ በጠቅላላው ፡ የተሻለ ፡ ፍትሕ ፡ የሚሰጥ ፡ ይመስላል ። [21]

ይሁን ፡ እንጂ ፡ የሕግና ፡ የሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ልዩነት ፡ በ፩ኛው ፡ ጉዳይ ፡ ለቀረበው ፡ ችግር ፡ መፍትሔ ፡ አያስገኝም ። ፩ኛው ፡ ጉዳይ ፡ የመንግሥት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ተሻሽሎ ፡ ከወጣው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ጋር ፡ ተቃራኒ ፡ በሆኑ ፡ ከ፲፱፻፹፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በፊት ፡ በታወጁ ፡ አዋጆች ፡ መሠረት ፡ እንዲሠሩ ፡ ይፈቅድላቸዋልን ፡ የሚል ፡ ጥያቄ ፡ በቀጥታ ፡ ያቀርባል ።

አንቀጽ ፡ ፸፰ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ በሚፈጸሙ ፡ የመንግሥት ፡ ተግባሮች ፡ እንዲገታ ፡ የተደረገበት ፡ ዓላማ ፡ መስሎ ፡ የሚታየውን ፡ እንዲያረካ ፡ ከተፈለገ ፡ ጥያቄው ፡ በአዎንታ ፡ ካልሆነ ፡ በሌላ ፡ እንዴት ፡ እንደሚመለስ ፡ ለማየት ፡ አደጋች ፡ ነው ። ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አያሌ ፡ በሆኑ ፡ የመንግሥት ፡ ተግባሮች ፡ ላይ ፡ የማያገለግል ፡ መሆኑ ፡ አለጥርጥር ፡ ለአንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ከተለመደው ፡ የተዛባ ፡ ነገር ፡ መስሎ ፡ ይታያቸዋል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ በአንቀጽ ፡ ፸፰ ፡ ተፈላጊ ፡ መስሎ ፡ የሚታየው ፡ ይኸው ፡ መዛባት ፡ ነው ፤ ማለት ፡ የተፈለገው ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ከመታወጁ ፡ በፊት ፡ የታወጁ ፡ አዋጆችና ፡ ድንጋጌዎች ፡ እንደ ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ሕግ ፡ ሁነው ፡ እንዲቀጥሉ ፡ ነው ።

---

21 እላይ ፡ በ፲፯ኛው ፡ ተራ ፡ ቍጥር ፡ የግርጌ ፡ ማስረጃ ፡ በተጠቀሰው ፡ ክስ ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሕግ ፡ ክፍል ፡ ማስታወቂያ ፡ አንቀጽ ፡ ፯ ፡ ቍ ፡ ፻፲፪ን ፡ (፲፱፻፵) ፡ ወደ ፡ ጐን ፡ ትቶ ፡ የማዘጋጃ ፡ ቤትን ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ውሳኔ ፡ በይግባኝ ፡ መርምሮአል ። ነገር ፡ ግን ፡ አንቀጽ ፡ ፸፰ ፡ ለወደፊት ፡ ስለሚደረጉ ፡ የመንግሥት ፡ ውሳኔዎች ፡ የመሠረተውን ፡ ወሰን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ያሻሻለበት ፡ ምክንያት ፡ አልተገለጸም ። ደግሞም ፡ የይግባኙ ፡ ክርክር ፡ ስለ ፡ አዋጁ ፡ ትርጉም ፡ ብቻ ፡ ስለነበር ፡ የፍርድ ፡ ቤቶችን ፡ ሥልጣን ፡ የሚወስነውን ፡ ጉዳይ ፡ ወደ ፡ ጐን ፡ ለመተው ፡ የቀረበውን ፡ ክርክር ፡ በመጠኑ ፡ ሊያደክመው ፡ ይችላል ።

የአንቀጽ ፡ ፻፳፪ ፡ ወደፊት ፡ በሚፈጸሙ ፡ የመንግሥት ፡ ተግባሮች ፡ መገታት ፡ ትርጉም ፡ ይህ ፡ ካልሆነ ፡ ጥቅሙ ፡ ጠባብ ፡ ነው ፤ ያስወግዳልም ፡ ተብሎ ፡ ከታሰበው ፡ ችግር ፡ ይበልጥ ፡ የተወሰነ ፡ ነው ፤ አብዛኛዎቹ ፡ ጠቃሚ ፡ የመንግሥት ፡ ተግባሮች ፡ ዋና ፡ ነገር ፡ የሆኑበት ፡ ምክንያት ፡ በመሠረቱ ፡ ወደፊት ፡ ለሚፈጸሙ ፡ የመንግሥት ፡ ተግባሮች ፡ መመሪያ ፡ በመሆናቸው ፡ ነው ። የአንድ ፡ የግብር ፡ አዋጅ መታወጅና ፡ አንድ ፡ ወንጀለኛ ፡ ለተወሰነ ፡ የእሥራት ፡ ጊዜ ፡ እንዲታሠር ፡ መፍረድ ፡ የመንግሥት ፡ ተግባሮች ፡ ናቸው ። ግን፡ ከፍተኛ ፡ ነገር ፡ የሚሆኑት ፡ ሌሎች፡ የመንግሥት ፡ ተግባሮች ፡ ይከተሉአቸዋል ፡ ተብሎ ፡ ስለሚጠበቅ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ግብር ፡ ሰብሳቢዎች ፡ በአዋጁ ፡ በታዘዘው ፡ አኳኋን ፡ ግብር ፡ እንደሚሰበስቡ ፡ ይጠበቃል ። የወህኒ ፡ ቤት ፡ ባለሥልጣኖችም ፡ እሥረኛውን ፡ በፍርድ ፡ ለተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ በእሥር ፡ ቤት ፡ እንደሚያቆዩት ፡ እምነት ፡ ሊጣልባቸው ፡ ይቻላል ።

መሪ ፡ የመንግሥት ፡ ተግባሮች ፡ ከተከታታዩና ፡ ዘላቂ ፡ ከሆነው ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ከማዋል ፡ አድራጎት ፡ ጋር ፡ እንዲህ ፡ ማቀናበር ፡ በመላው ፡ ሕግና ፡ በአስተዳደር ፡ ተግባር ፡ ይሠራጫል ። መሪ ፡ የሆነው ፡ ተግባር ፡ ተገቢነትም ፡ በመሪው ፡ ተግባር ፡ የተፈለገውን ፡ ነገር ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ በማዋል ፡ ከሚፈጸመው ፡ አድራጎት ፡ ተገቢነት ፡ ሊለይ ፡ አይችልም ። በአዋጁ ፡ የተጠየቀው ፡ ተግባር ፡ ዋጋ ፡ የሌለውና ፡ የማያገለግል ፡ ከሆነ ፡ አዋጁም ፡ እንዲሁ ፡ ዋጋ ፡ የሌለውና ፡ የማያገለግል ፡ ነው ።

በሥራ ፡ ላይ ፡ እንዳያውሉት ፡ የመንግሥት ፡ ባለሥልጣኖችን ፡ በመከልከል ፡ ከ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በፊት ፡ የነበረን ፡ አዋጅ ፡ ውጤት ፡ በሚሰጥ ፡ አኳኋን ፡ ዋጋ ፡ አልባ ፡ ለማድረግ ፡ ከተቻለ ፡ ከ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በፊት ፡ የተፈረደ ፡ የወንጀል ፡ እሥራትም ፡ እንደዚሁ ፡ እሥራቱ ፡ ስለ ፡ ቀጠለ ፡ በወህኒ ፡ ቤት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ላይ ፡ በሚሰነዘር ፡ ክስ ፡ ተገልባጭ ፡ የማይሆንበት ፡ ምክንያት ፡ ግልጽ ፡ አይደለም። ይህንንም ፡ ማለት ፡ ከ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በፊት ፡ በነበረ ፡ አዋጅ ፡ መሠረት ፡ የተፈጸመ ፡ ማናቸውም ፡ የመንግሥት ፡ አድራጎት ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ በሆነ ፡ ምክንያት ፡ ከመጠየቅ ፡ ነጻ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ አይደለም ። አብዛኛዎቹ ፡ አዋጆች ፡ በተለይም ፡ በጣም ፡ ቀደምትነት ፡ ያላቸው ፡ አዋጆች ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ስለሚውሉበት ፡ ሁናቴ ፡ እምብዛም ፡ አይናገሩ ። በደንቦች ፡ ወይም ፡ በአስተዳደር ፡ አስተያየት ፡ የሚሞሉ ፡ ብዙ ፡ ክፍት ፡ ነገሮች ፡ ተትተዋል ። አዋጁ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ሊውል ፡ የሚችልበት ፡ ሌላ ፡ መንገድ ፡ ከኖረ ፡ እነዚህ ፡ ደንቦች ፡ ወይም ፡ አስተያየቶች ፡ ራሳቸውን ፡ እንደ ፡ ቻሉ ፡ የመንግሥት ፡ ተግባር ፡ ሊቆጠሩና ፡ የአዋጁም ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ሳይነካ ፡ ሊሻሩ ፡ ይቻላል ።

ከዚህም ፡ በላይ ፡ የአንድ ፡ ከ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በፊት ፡ የታወጀ ፡ አዋጅ ፡ ፍች ፡ የሚያሻማ ፡ ሲሆን ፡ የአዋጁን ፡ ከሕገ ፡ መንግሥት ፡ ደረጃ ፡ መጋጨት ፡ የሚያሳንስ ፡ ፍች ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለመምረጥ ፡ ይችላል ። በእንደዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ አተረጓጎምና ፡ አድራጎቱ ፡ በቀድሞው ፡ አዋጅ ፡ እርግጥ ፡ መፈለጉን ፡ በጥንቃቄ ፡ በመመርመር ፤ በኋላ ፡ የሚታወጁ ፡ ሕጎችም ፡ እየበዙ ፡ እንደመሄዳቸው ፡ መጠን ፤ ከ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በፊት ፡ የታወጁ ፡ አዋጆች ፡ አስፈላጊነት ፡ እያነሰ ፡ የሚሄድ ፡ በመሆኑና ፡ የቀድሞዎቹ ፡ ሕጎች ፡ በአዲሶቹ ፡ እየተሻሩና ፡ እየታገዱ ፡ በመቅረታቸው ፡ ምክንያት ፡ በአንቀጽ ፡ ፻፳፪ ፡ የተፈጠረው ፡ "ከተለመደው ፡ የተዛባ ፡ ሁናቴ ፡ በአነስተኛና ፡ እየጠበበ ፡ በሚሄድ ፡ አድማስ ፡ ሊወሰን ፡ ይቻላል ።"

## ያለማስረጃ፡የተቀበልነው፡መልስ፡—የሁለቱ፡ሕገ፡መንግሥቶች፡ችግሮች።

የአስተዳደር፡አድራጎቶችን፡በፍርድ፡ቤት፡እንደገና፡የማየት፡ሕገ፡መንግሥታዊ፡የሆነ፡ሥልጣን፡ጥያቄ፡"ተገቢ፡የሕግ፡ሥነ፡ሥርዓት"፡ (due Proces oflaw) በሚለው ፡ አነጋገር ፡ ፍች ፡ እንዳይቀርብ ፡ የሚሰጠው ፡ ዋና ፡ መቃወሚያ ፤ የተገቢው ፡ የሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ መብት ፡ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ መሰጠት ፡ የተረጋገጠ ፡ ነገር ፡ አለመሆን ፡ ነው ። የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በተመሳሳይ ፡ አማርኛና ፡ እንግሊዝኛ ፡ ጽሑፎች ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ የታተመ ፡ ሲሆን ፡ የአንቀጽ ፡ ፵፫ ፡ እንግሊዝኛ ፡ ጽሑፍ ፡ ተገቢ ፡ የሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓትን ፡ መብት ፡ በተባበረው ፡ የአሜሪካ ፡ መንግሥት ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ በተገለጸው ፡ አነጋገር ፡ ዓይነት ፡ የሚጠብቅ ፡ ይመስላል ።

> "ማንኛውም ፡ ሰው ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ሕይወቱን ፡ ነጻነቱን ፡ ወይም ፡ንብረቱን ፡ <u>ያለተገቢ ፡ ሕጋዊ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት</u>* ፡ አያጣም ።" (የተሻሻለው ፡ ሕገ፡ መንግሥት፡ አንቀጽ፡ ፵፫፡ የእንግሊዝኛው፡ ጽሑፍ) ፡

> "ማንኛውም ፡ ሰው ፡— . . . ሕይወቱን ፡ ነጻነቱን ፡ ወይም ፡ ንብረቱን ፡ ያለ ተገቢ ፡ የሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ አያጣም ።" የተባበረው ፡ የአሜሪካ ፡ መንግሥት ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ፭ኛው ፡ ማረሚያ ፡ [22]

ነገር ፡ ግን ፡ እንደ ፡ መደበኛ ፡ ሕግ ፡ የሚቆጠረው ፡ [23] የአንቀጽ ፡ ፵፫ ፡ የአማርኛው፡ ጽሑፍ ፡ ቋንቋ ፡ ጥቂት ፡ የተለየ ፡ ሆኖ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡—

> "ማንኛውም ፡ ሰው ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ሕይወቱን ፡ ነጻነቱን ፡ ወይም፡ ንብረቱን ፡ <u>ያለ ፡ ሕግ</u>፡ አያጣም" ።

በዚህ ፡ ልዩነት ፡ የተነሣ ፡ ሁለት ፡ ፍችዎች ፡ ይፈጠራሉ ። የመጀመሪያው ፡ አንቀጽ ፡ ፵፫ ፡ በተባበረው ፡ የአሜሪካ ፡ መንግሥት ፡ የተስፋፋውን ፡ የተገቢ ፡ የሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ መንፈስ ፡ አጠቃሎ ፡ እንዲይዝ ፡ ተፈልጓል ፤ በአማርኛው ና ፡ በእንግሊዝኛው ፡ እትም ፡ መካከል ፡ ያለውም ፡ ልዩነት ፡ የሚገልጠው ፡ ረቂቅ ፡ የሕግ ፡ ሐሳቦችን ፡ ለመተርጐም ፡ ምን ፡ ያህል ፡ አዳጋች ፡ መሆኑን ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ የሚል ፡ ፍች ፡ ነው ። የዚህ ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ የሆነ ፡ ሚዛን ፡ በዝርዝር ፡

---

22 አምስተኛው ፡ ማሻሻያ ፡ የፌዴራል ፡ መንግሥት ፡ ተግባሮችን ፡ ብቻ ፡ የሚመለከት ፡ ነው ። በ፲፬ኛው ፡ ማሻሻያ ፡ ክፍል ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ የእስቴቶችን ፡ መንግሥት ፡ ተ ግባር ፡ የሚመለከት ፡ በሞላ፡ ጐደል ፡ ተመሳሳይ ፡ የሆነ ፡ አንቀጽ ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ውስጥ ፡ ተጨምሮአል ።

23 ኤስ ፡ ሎዊንሽተይን ፡ <u>ማቴሪያልስ ፡ ፎር ፡ ዘ ፡ ስተዲ ፡ ኦፍ ፡ ዘ ፡ ፒናል ፡ ሎው ፡ ኦፍ ፡ ኢትዮጵያ</u> ፡ (፲፱፻፷፭ ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ ገጽ ፡ ፫፻፹፩ ፤) እንዲሁም ፡ ጂ ፡ ክሽችኖቪች ፡ "ኢትዮጵያን ፡ ሊጋል ፡ ኢጅኬሽን" ፡ <u>የኢትዮጵያ ፡ የጥናትና ፡ የምርምር ፡ መጽሔት</u> ፡ ቮሊዩም ፡ ፩ ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ (፲፱፻፷፫ ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፤ ገጽ ፡ ፷፫ ፡ እና ፡ ፷፬ ፡ ይመለከቷል) ። በ፲፱፻፵፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ፭ኛው ፡ ዓመት ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ስለ ፡ ዳኝነት ፡ ሥራ ፡ አካሄድ ፡ በወጣው ፡ አዋጅ ፡ ቍጥር ፡ ፳፱ ፡ አንቀጽ ፡ ፳፱ ፡ መሠረት ፡ ሕጎች ፡ በአማርኛና ፡ በእንግሊዝኛ ፡ መታተም ፡ እንዳለባቸው ፡ ሲገልጽ ፡ ሁለቱ ፡ ባልተስማሙ ፡ ጊዜ ፡ የትኛው ፡ እንደሚያይል ፡ (እንደሚረታ) ፡ አልተጠቀሰም ። በአማርኛ ፡ የወጣው ፡ ሕግ ፡ ያይላል ፤ የሚል ፡ የግምት ፡ አስተያየት ፡ በሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፻፳፭(ለ) የተመሠረተ ፡ ይመስላል ። በዚህም ፡ አንቀጽ ፡ መሠረት ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ መደበኛ ፡ ኦፍሲየል ፡ ቋንቋ ፡ አማርኛ ፡ ነው ። በ፲፱፻፳፫ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ወይም ፡ በ፲፱፻፵፰ ፡ ተሻሽሎ ፡ ከወጣው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በፊት ፡ ተመሳሳይ ፡ ድንጋጌ ፡ የያዘ ፡ ሌላ ፡ ሕግ ፡ ስለአልነበረ ፡ ከ፲፱፻፳፫ ፡ እስከ ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በነበረው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የሁለቱ ፡ ቋንቋዎች ፡ ሕጋዊ ፡ አቋም፡ ከ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በኋላ ፡ ካለው ፡ አቋም ፡ ጋር ፡ ተመሳሳይ ፡ አይደለም ።

ሁናቴው ፡ በተባበረው ፡ የአሜሪካ ፡ መንግሥት ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ ከሚ ገኘው ፡ ተገቢ ፡ የሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ጋር ፡ መመሳሰል ፡ ወይም ፡ አለመመሳሰል፡ ለያዝነው ፡ ክርክር ፡ ጥቅም ፡ የለውም ። ዋናው ፡ ነገር ፡ ከተራ ፡ አዋጆች ፡ የበላይ ነት ፡ ያለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ ሚዛን ፡ መሆኑ ፡ ነው ።

ሁለተኛው ፡ ፍች ፤ የአማርኛው ፡ ጽሑፍ ፡ አሁን ፡ እንዳለ ፡ የተፈለገውን ፡ ሐሳብ ፡ በሚገባ ፡ ይገልጻል ፤ ሕይወት ፡ ነጻነት ፡ ወይም ፡ ንብረት ፡ ያለሕግ ፡ ማለት ፡ ሕግ ፡ በሚያዘው ፡ መሠረት ፡ ካልሆነ ፡ መወሰድ ፡ የለበትም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የሕጉ ፡ ትእዛዝ ፡ ምን ፡ እንደሚሆን ፡ ወሰን ፡ አልተሰጠውም ፡ የሚል ፡ ነው ። በመጀመሪያው ፡ ፍች ፡ ንብረትን ፡ ለመንሣት ፡ የሚቃጣ ፡ እርምጃ ፡ ሁለት ፡ ጥያቄዎችን ፡ ያስነሳል ። የተወሰደው ፡ እርምጃ ፡ ጉዳዩ ፡ የሚመለከተው ፡ ሕግ ፡ በሚያዘው ፡ መሠረት ፡ ተፈጽሟልን? የሕገ ፡ መንግሥቱንስ ፡ ሚዛን ፡ አርክቷልን? በሁለተኛ ፡ ፍች ፡ ግን ፡ የሚነሣው ፡ ጥያቄ ፡ የመጀመሪያው ፡ ብቻ ፡ ነው ።

እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ይህን ፡ የአተረጓጐም ፡ ጥያቄ ፡ በሚመለከት ፡ በአውራ ፡ ጐዳና ፡ ባለሥልጣንና ፡ በመብራቱ ፡ ፍሥሐ ፡ መሐከል ፡ [24] በነበረው ፡ ክርክር ፡ ላይ ፡ የተሰጠ ፡ አንድ ፡ የጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔ ፡ ታትሞ ፡ ወጥቷል ። እዚያ ፡ ላይ ፡ ጉዳዩ ፡ የቀረበለት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ክፍል ፡ በአንድ ፡ አዋጅ ፡ መሠረት ፡ የተፈጸመ ፡ ማናቸውም ፡ አድራጎት ፡ በአንቀጽ ፡ ፵፫ ፡ [25] መሠ ረት ፡ ተገቢ ፡ እንዳልሆነ ፡ ሊቆጠር ፡ አይችልም ፡ በማለቱ ፡ ሁለተኛውን ፡ ፍች ፡ የተቀበለ ፡ ይመስላል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ አንቀጽ ፡ ፵፫ ፡ አንድ ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ የሆነ ፡ ደረጃ ፡ ይፈጥራል ፡ በሚለው ፡ አስተያየት ፡ መሠረት ፡ የተሰጡ ፡ አያሌ ፡ የጠቅላይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ውሳኔዎች ፡ ይገኛሉ ። [26]

አንቀጽ ፡ ፵፫ ፡ የሚያመለክተውን ፡ ሐሳብ ፡ በሚገባ ፡ የመመርመር ፡ ተግ ባር ፤ እንደሰማሁት ፤ በቃል ፡ ለቃል ፡ አተረጓጐምም ፡ ሆነ ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ በወጣው ፡ እንግሊዝኛ ፡ ጽሑፍ ፡ ያልተመለከቱትን ፡ [27] በአማርኛው ፡ ጽሑፍ ፡ የተሠራባቸውን ፡ ቃላት ፡ ረቂቅ ፡ ልዩነቶች ፡ በማጥናት ፡ ላይ ፡ በከፊል ፡ ያርፋል ። ይህን ፡ ዓይነቱ ፡ አመራመር ፡ ከችሎታዬ ፡ በላይ ፡ ስለሆነ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ የሚከተ ለው ፡ ክርክር ፡ ጥያቄውን ፡ በከፊል ፡ የሚመረምርና ፡ ለጊዜው ፡ የሚያገለግል ፡ ብቻ ፡ ከመሆን ፡ አያልፍም ። ቢበዛ ፡ ሊመለከቷቸው ፡ የሚገባውን ፡ አስረጅ ፡ ሃሳ ቦች ፡ ያመለክት ፡ ይሆናል ።

ከመጀመሪያው ፡ መታወቅ ፡ የሚገባው ፤ ምንም ፡ እንኳን ፡ ከሁለተኛው ፡ ፍችው ፡ በመጀመሪያ ፡ ፍችው ፡ የበለጠ ፡ ዋጋ ፡ ቢኖረው ፤ አንቀጽ ፡ ፵፫ ፡ ዋና ፡ የሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ማስከበሪያ ፡ ዋስትና ፡ መሆኑ ፡ ነው ። "ያለሕግ" ፡ በሚለው ፡ አነጋገር ፡ ውስጥ ፡ የ"ሕግ" ፡ ፍች ፡ ማንኛውም ፡ ቢሆን ፡ ቢያንስ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡

---

24 የ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ፩ኛ ፡ ቮሊዩም ፡ ገጽ ፡ ፴፫—፴፬ ፡

25 ጉዳዩን ፡ በጥብቅ ፡ ብንመረምር ፡ የቀረበለት ፡ ሕግ ፡ ማለት ፡ አዋጅ ፡ ቍጥር ፡ ፻፲፭ ፡ ከተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በፊት ፡ የወጣ ፡ ስለሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይህን ፡ ክርክር ፡ አንሥቶ ፡ መመርመር ፡ የሚገባው ፡ አይመስልም ።

26 በከሳሽ ፡ በአቶ ፡ እገሌ ፤ በተከሳሽ ፡ የፖስታ ፡ ቴ ፡ ቴ ፡ ሚኒስቴር ፡ (ከፍተኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፤ ፲፱፻፶፩ ፡ ዓ ፡ ም) ፡ መካከል ፡ የነበረውን ፡ ክርክር ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ቮልዩም ፡ ፪ ፤ ገጽ ፡ ፫፻፷፩ ፡ ይመለከቷል ፤ እላይ ፡ በግርጌ ፡ ማስታወሻ ፤ የተጠቀሰውን ፡ በከሳሽ ፡ የገንዘብ ፡ ሚኒ ስቴር ፡ ነገረ ፡ ፈጅ ፡ በተከሳሽ ፡ በሚስተር ፡ ሳሪስ ፡ መካከል ፡ የነበረውን ፡ ክርክር ፡ ያወዳድሯል ፤ እላይ ፡ በግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ፲፯ ፡ የተጠቀሰውን ፡ በከሳሽ ፡ ሻህ ፡ እና ፡ በተከሳሽ ፡ የአዲስ ፡ አበባ ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ የገንዘብ ፡ ዘበኛ ፡ ክፍል ፡ የነበረውን ፡ ክርክር ፡ ይመለከቷል ።

27 በሕጉ ፡ የአማርኛ ፡ ቃላት ፡ አግባብ ፡ የሚሰጠው ፡ ትርጉም ፡ ያልተጠናበት ፡ ምርምር ፡ የተሟላ ፡ ሊሆን ፡ እንደማይችል ፡ ለገለጸልኝ ፡ የሦስተኛ ፡ ዓመት ፡ የሕግ ፡ ተማሪ ፡ ለሆነው ፡ ለአቶ ፡ ሰላሙ ፡ በቀለ ፡ ምስጋናዬን ፡ ልገልጽ ፡ እወዳለሁ ።

የተነገረ ፡ የውሳኔ ፡ ደንብ ፡ መሆን ፡ አለበት ። ይህም ፡ ራሱ ፡ በዘፈቀደ ፡ ከሚፈጸም ፡ የመንግሥት ፡ አድራጎት ፡ ታላቅ ፡ መከላከያ ፡ ነው ። [28]

የመጀመሪያውን ፡ ፍች ፡ ለመደገፊያ ፡ ጉልህ ፡ ሆኖ ፡ የሚታየው ፡ ክርክር ፡ በተለይም ፡ በተባበረው ፡ የአሜሪካ ፡ መንግሥት ፡ ለተማረ ፡ ሕግ ፡ አዋቂ ፡ የአንቀጽ ፡ ፶፫ ፡ ከተባበረው ፡ የአሜሪካ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ተነጻጻሪ ፡ አንቀጽ ፡ ጋር ፡ መመሳሰል ፡ ነው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ በዚህ ፡ አስተያየት ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ክርክርን ፡ እግቡ ፡ ለማድረስ ፡ በአማርኛው ፡ ጽሑፍና ፡ በተባበረው ፡ የአሜሪካ ፡ መንግሥት ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ተመሳሳይ ፡ አንቀጽ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ልዩነት ፡ የተፈጠረው ፡ ከእንግሊዝኛ ፡ ወደ ፡ አማርኛ ፡ በመተርጐም ፡ ላይ ፡ ባለ ፡ ችግር ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ የክርክር ፡ ነጥብ ፡ መያዝ ፡ አለብን ። ግን ፡ አንቀጽ ፡ ፶፫ ፡ ከሌሎች ፡ የሕዝብ ፡ መብት ፡ አንቀጾች ፡ ጋር ፡ ሲታይ ፡ የዚህ ፡ ነጥብ ፡ እውነተኛ ፡ መሆን ፡ ጉልህነቱን ፡ ይቀንሳል ። ከአንቀጽ ፡ ፶፫ ፡ ሌላ ፡ ስምንት ፡ ተመሳሳይ ፡ አንቀጾች ፡ በአንድ ፡ በኩል ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ በሕግ ፡ መሠረት ፡ በሚል ፡ ተመሳሳይ ፡ ንውስ ፡ ሐረግ ፡ ተገትተዋል ።

“. . . በሕግ ፡ መሠረት ፡* የሃይማኖታቸውን ፡ ሥርዓት ፡ አክብረው ፡ በነጻ ፡ ከመፈጸም ፡ አይከለከሉም ።” (አንቀጽ ፡ ፶)

“በመላው ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ በሕግ ፡ መሠረት ፡ የንግግርና ፡ የጋዜጣ ፡ ነጻነት ፡ የተፈቀደ ፡ ነው ።” (አንቀጽ ፡ ፶፩)

“ማንኛውም ፡ ሰው ፡ በሕግ ፡ የተወሰነውን ፡ ሳይተላለፍ ፡ ንብረትን ፡ ለማበጀትና ፡ በፈቀደው ፡ ለማዋል ፡ መብት ፡ አለው ።” (አንቀጽ ፡ ፶፪)

“የኢትዮጵያ ፡ ዜጎች ፡ በሕግ ፡ ተዘርዝሮ ፡ በሚወሰነው ፡ መሠረት ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ሳይዙ ፡ ሰላማዊ ፡ ስብሰባ ፡ ለማድረግ ፡ መብት ፡ አላቸው ።” (አንቀጽ ፡ ፶፭)

“በሕግ ፡ ካልተከለከለ ፡ በቀር ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ ከስፍራ ፡ ወደ ፡ ስፍራ ፡ የመዘዋወርና ፡ መኖሪያ ፡ ስፍራን ፡ የመለወጥ ፡ ነጻነት ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ዜጎች ፡ ሁሉ ፡ ተረጋግጧል ።” (አንቀጽ ፡ ፶፮)

“ማንኛውም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜጋ ፡ በሕግ ፡ መሠረት ፡ ማናቸውንም ፡ ዓይነት ፡ ሥራ ፡ እየሠራ ፡ ለመኖር ፤ ማናቸውንም ፡ የሥራ ፡ ማኅበር ፡ ለማቋቋምና ፡ በማናቸውም ፡ ማኅበር ፡ አባል ፡ ለመሆን ፡ መብት ፡ አለው ።” (አንቀጽ ፡ ፶፯)

“ቅጣት ፡ የሚፈጸመው ፡ በአጥፊው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ሕግ ፡ እንደሚፈቅደው ፡ ካልሆነና ፡ ያደረገው ፡ ጥፋት ፡ ካልተረጋገጠ ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ አይቀጣም ።” (አንቀጽ ፡ ፶፱)

“ማናቸውም ፡ ሰውና ፡ ማናቸውም ፡ የግል ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ ያለሕግ ፡ መበርበርም ፤ መያዝም ፡ የለበትም ።” (አንቀጽ ፡ ፷፩) ፡ በየአንዳንዱ ፡ አንቀጽ ፡ ውስጥ ፡ የተሰመረባቸው ፡ ለአጋኖ ፡ ነው ።

28 ከኤል ፡ ፋለር ፤ ዘ ፡ ሞራሊቲ ፡ ኦፍ ፡ ሎው ፤ (፲፱፻፷፬ ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ) ፡ ምዕራፍ ፡ ፪ ፡ ጋር ፡ ማስተያየት ፡ ያሻል ።

በተለይ ፡ አንቀጽ ፡ ፵፩ና ፡ ፵፪ ፡ በምንም ፡ ዓይነት ፡ ተመሳሳይ ፡ ንዑስ ፡ ሐረግ ፡ ካልተገቱት ፡ [29] የተባበረው ፡ የአሜሪካ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጾች ፡ ጋር ፡ ስለሚመሳሰሉ ፡ የነዚህ ፡ አንቀጾች ፡ አነጋገር ፡ "ለጥያቄው ፡ መፍትሔ ፡ ለማግኘት ፡ የተባበረው ፡ የአሜሪካ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽን ፡ መመልከት ፡ በራሱ ፡ በቂ ፡ ነው ፤" የሚለው ፡ ቀለል ፡ ያለ ፡ አስተያየት ፡ ተቀባይነት ፡ እንዳያገኝ ፡ ማድረጉ ፡ አይቀርም ። ሆኖም ፡ በአንድ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ የነዚህ ፡ አንቀጾች ፡ አነጋገር ፡ ለሁለተኛው ፡ ፍችም ፡ ቢሆን ፡ አጥጋቢ ፡ ማስረጃ ፡ ከማቅረብ ፡ እጅግ ፡ የራቀ ፡ ነው ። ይህ ፡ ልዩነት ፡ በአንቀጽ ፡ ፵፫ ፡ ውስጥ ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ የሆነ ፡ ደረጃ ፡ እንዳይኖር ፡ ለማድረግ ፡ መፈለጉን ፡ ለማመልከት ፡ አለመቻሉን ፡ ከሚገልጡት ፡ ምክንያቶች ፡ ጥቂቶቹ ፡ የተመሠረቱት ፡ ሁሉም ፡ በቃል ፡ ለቃል ፡ አተረጓጐም ፡ "ሕጎች" ፡ በሚለው ፡ ወደ ፡ እንግሊዝኛ ፡ ሊተረጐሙ ፡ በሚችሉት ፡ በአማርኛ ፡ ቃላት ፡ መካከል ፡ ባሉት ፡ ረቂቅ ፡ ልዩነቶች ፡ ነው ። ከአማርኛ ፡ ወደ ፡ እንግሊዝኛ ፡ ቃል ፡ ለቃል ፡ የተተረጐመውን ፡ ብንቀበለውም ፡ እንኳን ፡ ለመጀመሪያው ፡ ፍች ፡ በሚገባ ፡ ለመከራከር ፡ ይቻላል ።

በሕገ ፡ መንግሥት ፡ አግባባቸው ፡ ውስጥ ፡ የ"ሕጎች" ፡ ፍች ፡ የሚያሻማ ፡ ነው ። አዋጆችን ፡ ሁሉና ፡ የአስተዳደር ፡ ደንቦችን ፡ አጠቃልሎ ፡ እንደሚይዝ ፡ ሊነበብ ፡ ይችላል ፤ ግን ፡ ጠበብም ፡ ያለ ፡ ፍች ፡ በመስጠት ፡ ሊነበብ ፡ ይችላል ። የአመጣጡን ፡ ታሪክ ፡ ስንመረምር ፡ አንቀጽ ፡ ፵፫ ፡ የተወረሰው ፡ ከተባበረው ፡ የአሜሪካ ፡ መንግሥት ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ተመሳሳይ ፡ አንቀጽ ፡ ከሆነ ፡ አንቀጽ ፡ ፵፫ ፡ ለዚህ ፡ የአሜሪካ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ምንጭ ፡ ለሆነው ፡ "ለማግና ፡ ካርታ" ፡ ምዕራፍ ፡ ፴፱ ፡ ደግሞ ፡ ቀጥታ ፡ ተወላጅ ፡ መሆኑ ፡ ነው ። ምዕራፍ ፡ ፴፱ም ፡ "በአገሩ ፡ (በምድሩ) ፡ ሕግ ፡ መሠረት" ፡ (ፐር ፡ ሌጌም ፡ ቴሪ) ፡ ይላል ፡ እንጂ ፡ ስለ ፡ "ተገቢ ፡ የሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት" ፡ (ዲዩ ፡ ፕሮሴስ ፡ ኦፍ ፡ ሎው) ፡ አያነሣም ። [30] ከዚህም ፡ በላይ ፡ ራሱም ፡ "ተገቢ ፡ የሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት" ፡ ቢሆን ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ ሲነበብ ፡ ለባለ ፡ ጉዳዩ ፡ ከሚገባው ፡ በሕግ ፡ ከታዘዘ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በላይ ፡ ትርጉም ፡ የለውም ። ተገቢው ፡ የሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት/ የሚለው ፡ አነጋገር ፡ አሁን ፡ የያዘውን ፡ ልዩ ፡ ትርጉም ፡ እስከ ፡ አገኘ ፡ ድረስ ፤ ሕግ ፡ በልማዳዊ ፡ አነጋገር ፡ መንፈሱና ፡ ሕግ ፡ አጋጊውና ፡ የመንግሥት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ በተለምዶ ፡ ሥልጣናቸው ፡ ሲሠሩ ፡ ሊደርሱበት ፡ በማይችሉት ፡ መሠረታዊ ፡ ሐሳብ ፡ መንፈሱ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ልዩነት ፤ በማያሻማና ፡ በአጭር ፡ አነጋገር ፡ ለመግለጽ ፡ የሚያስችል ፡ ዘይቤ ፡ በእንግሊዝኛ ፡ ለማግኘት ፡ ባስቸገረ ፡ ነበር ። ይህን ፡ መሳይ ፡ ችግር ፡ አሁን ፡ በአማርኛው ፡ ቢገኝ ፡ የሚያስገርም ፡ ሊሆን ፡ አይገባም ።

---

29 በአንቀጽ ፡ ፵ና ፡ ፵፭ ፡ እንዲሁም ፡ በሌሎች ፡ አንቀጾች ፡ የተሰጡ ፡ የግል ፡ መብቶች ፡ በቀጥታ ፡ ከተባበረው ፡ የአሜሪካ ፡ መንግሥት ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ የተወሰዱ ፡ ናቸው ፤ ማለት ፡ አይደለም ። አብዛኞቹ ፡ መብቶች ፡ እላይ ፡ በ፶ኛው ፡ የግርጌ ፡ ማስረጃ ፡ በተጠቀሰው ፡ የፌዴራል ፡ ሕግ ፡ አማካይነት ፡ ከ፲፱፻፵፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በፊት ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ገብተዋል ፡ በ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በአዋጅ ፡ ቍጥር ፡ ፻፴፱ ፡ ስለ ፡ ሕዝባዊ ፡ መብት ፡ በ፲፫ኛ ፡ ዓመት ፡ ቍጥር ፡ ፫ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፤ እንዲሁም ፡ የኤርትራን ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ይመለከቷል ።

30 "ነጻነት ፡ ያለው ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ የአገር ፡ ሽማግሌ ፡ አይቶበት ፡ በሕግ ፡ ካልተፈረደበት ፡ ወይም ፡ ባገሩ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ካልሆነ ፡ በስተቀር ፡ አይያዝም ፡ ወይም ፡ አይታሠርም ፡ ወይም ፡ ንብረቱ ፡ አይነጠቅም ፡ ወይም ፡ ከሕግ ፡ ድጋፍ ፡ ውጭ ፡ አይደረግም ፡ ወይም ፡ አገር ፡ ለቆ ፡ እንዲ ሰደድ ፡ ወይም ፡ በማንኛውም ፡ መንገድ ፡ እንዲደመሰስ ፡ አይደረግም ፡ እንዲሁም ፡ በቀጥታ ፡ እራሳችን ፡ ወይም ፡ በትእዛዝ ፡ እንዲገደድ ፡ አናደርግም ።"

ማግና ፡ ካርታ ፡ ምዕራፍ ፡ ፴፱ ፡ አር ፡ ፔሪ ፡ ዘ ፡ ሶርስ ፡ ኦፍ ፡ አውር ፡ ሊበርቲ ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ በተባለው ፡ መጽሐፍ ፡ ገጽ ፡ ፲፯ ፡ ውስጥ ፡ እንደጠቀሰው ፡ ሔንሪ ፡ ፫ኛ ፡ በ፲፪፻፳፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ እንደገና ፡ ማግና ፡ ካርታን ፡ ሲያወጣ ፡ ፳፱ኛ ፡ ምዕራፍ ፡ ሆኖ ፡ ወጥቷል ። በተጠቀሰው ፡ መጽሐፍ ፡ ገጽ ፡ ፳ ፡ ይመለከቷል ።

"ሕግ" ፡ ወይም ፡ ማንኛውም ፡ ሌላ ፡ ቃል ፡ ከተራ ፡ ወይም ፡ ከተለመደ ፡ ትርጉሙ ፡ የተለየ ፡ ሌላ ፡ ትርጉም ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ሊኖረው ፡ እንደሚችል ፡ ለማረጋገጥ ፡ አዳጋች ፡ አይደለም ። የሚያዳግተው ፤ "ሕግ ፡ አርቃቂው ፡ ያሰበው ፡ ተራ ፡ ወይም ፡ የተለመደ ፡ ትርጉሙን ፡ ነው ፤" የሚለውን ፡ እምነት ፡ ማሸነፉ ፡ ነው ። እዚህ ፡ ላይ ፡ "ሕግ" ፡ ከተለመደ ፡ ወይም ፡ ተራ ፡ ትርጉሙ ፡ የተለየ ፡ ትርጉም ፡ አለው ፡ ያልነውን ፡ የሚደግፉ ፡ ሁለት ፡ ምክንያቶች ፡ ቀርበዋል ። የመጀመሪያው ፡ ምክንያት ፡ ምናልባት ፡ ለአንቀጽ ፡ ፵፫ ፡ ምንጩ ፡ ሊሆን ፡ በሚችለው፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ሲሆን ፤ ሌላው ፤ አንቀጽ ፡ ፵፫ ፡ ከሌሎቹ ፡ የሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጾች ፡ ጋር ፡ ባለው ፡ ግንኙነት ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ነው ።

በ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ የተገቢ ፡ የሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ማለት ፡ የአንቀጽ ፡ ፵፫ ፡ መብት ፡ ዋስትና ፡ አልተጨመረም ። የተገቢ ፡ የሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ልማዳዊ ፡ ቋንቋ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ የታየው ፡ በመስከረም ፡ ወር ፡ ፲፱፻፵፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡[31] በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ በጸደቀው ፡ የፌዴራል ፡ ሕግ ፡ ይመስላል ። የፌዴራሉ ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፯(ሐ) ፡ "ንብረት ፡ የማበጀትና ፡ በፈቀደው ፡ የማዋልን ፡ መብት ፡ ዋስትና ፡ ለኤርትራ ፡ ዜጎች ፡ ሰጥቷል ። እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡—

"ማንም ፡ ሰው ፡ ንብረቱ ፤ የውል ፡ መብቱ ፡ ጭምር ፡ ያለተገቢ ፡ ሕጋዊ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓትና ፤ ትክክለኛና ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ ግምት ፡ ሳይከፈለው ፤ አይወሰድበትም ።"

በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ አለመታተሙን ፡ ስንመለከት ፤ የፌዴራሉ ፡ ሕግ ፡ እንደተለመደው ፡ እነጋገር ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ አይደለም ።[32] ከመጀመሪያው ፡ ኢትዮጵያና ፡ ኤርትራ ፡ በፌዴራሲዮን ፡ እንዲቀሳቀሱ ፡ ለማድረግ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መጽደቅ ፡ የነበረበት ፡ የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ውሳኔ ፡ (ሪዞሉሲዮን) ፡ ነበረ ። ስለዚህ ፡ የፌዴራሉን ፡ ሕግ ፡ ፍች ፡ ለማግኘት ፡ የሚሻ ፡ ሰው ፡ መመልከት ፡ የሚገባው ፡ ወደ ፡ አማርኛው ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፤ የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ጠቅላላ ፡ ስብሰባ ፡ ሥራ ፡ መምሪያ ፡ መደበኛ ፡ ቋንቋ ፡ ወደሆነው ፡ ወደ ፡ እንግሊዝኛም ፡ ጽሑፍ ፡ ጭምር ፡ ነው ። የአንቀጽ ፡ ፯(ሐ) ፡ እንግሊዝኛ ፡ ጽሑፍም ፡ ግልጽ ፡ በሆነ ፡ እነጋገር ፡ የተገቢ ፡ የሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓትን ፡ መብት ፡ ዋስትና ፡ ይሰጣል ።

የፌዴሬሺኑ ፡ መንግሥት ፡ ከተቋቋመ ፡ ከአንድ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ የሕዝብ ፡ መብቶች ፡ አዋጅ ፡[33] ታወጀ ። የአዋጁ ፡ አንቀጽ ፡ ፫ ፡ "ማናቸውም ፡ አስተዳደር ፡ ወይም ፡ ከፌዴሬሺኑ ፡ አስተዳደር ፡ ማናቸውም ፡ ክፍል ፡ የፌድዴሬሺኑን ፡ አስተዳደር ፡ የሀገር ፡ ተወላጆችን ፡ መብታዊ ፡ ጥቅም ፡ ወይም ፡ መብታዊ ፡ ነጻነት ፡ የሚቀንስ ፤ ወይም ፡ ሕግ ፡ በማይፈቅደው ፡ አኳኋን ፡ የማንኛውንም ፡ ሰው ፡ ሕይወት ፤ ነጻነት ፡ ወይም ፡ ንብረት ፡ የሚያሳጣ ፡ ሕግ ፡ አያወጣም ፤ ወይም ፡ ጸንቶ ፡ እንዲሠራበት ፡ አያደርግም ፤" የሚል ፡ ዋስትና፡ ይሰጣል ። የአንቀጽ ፡ ፫ ፡ አማርኛ፡ ጽሑፍ ፡ በአንቀጽ ፡ ፵፫ ፡ ውስጥ ፡ እንዳለው ፡ አሻሚ ፡ ትርጉም ፡ ያስነሣል ። ነገር ፡ ግን ፡ በአንቀጽ ፡ ፫ ፡ ውስጥ ፡ ይህ ፡ አሻሚ ፡ ትርጉም ፡ እንዴት ፡ መፈታት ፡ እንደ

31 ኋን ፡ ማሬን ፡ እላይ ፡ በ፮ኛ ፡ የግርጌ ፡ ማስረጃ ፡ በተጠቀሰው ፡ መጽሐፍ ፡ ፪ኛ ፡ አፔንዲክስ ፡ ይመለከቷል ።

32 እላይ ፡ በ፭ኛው ፡ የግርጌ ፡ ማስረጃ ፡ በተጠቀሰው ፡ በ፲፱፻፵፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የወጣው ፡ ትእዛዝ ፡ ቍጥር ፡ ፮ ፡ የፌዴራል ፡ አዋጅ ፡ መጽደቁን ፡ ይጠቅሳል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ደንቡ ፡ የጸደቀበት ፡ መግለጫ ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ አልወጣም ።

33 በ፳፱ኛ ፡ የግርጌ ፡ ማስረጃ ፡ ተጠቅሷል ።

ሚገባው ፡ ያለው ፡ ጥርጣሬ ፡ በጣም ፡ አነስተኛ ፡ ነው ። የአንቀጽ ፡ ፫ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ "ማናቸውም ፡ አስተዳደር ፡ . . . ሕግ ፡ አያወጣም ፡ ወይም ፡ ጸንቶ ፡ እንዲሠራበት ፡ አያደርግም" ፡ የሚለው ፡ አረፍተ ፡ ነገር ፡ ነው ። ይህ ፡ አረፍተ ፡ ነገር ፡ ሕይወትን ፡ ነጻነትን ፡ ወይም ፡ ንብረትን ፡ ያለ ፡ (ተራው) ፡ ሕግ ፡ ከማጣት ፡ ብቻ ፡ ዋስትና ፡ ጋር ፡ ከተያያዘ ፡ ዋስትናው ፡ ፍሬ ፡ ቢስ ፡ ይሆናል ፤ ወይም ፡ ይበልጥ ፡ በተስተካከለ ፡ አነጋገር ፡ ለመጠቀም ፡ ዋስትናው ፡ አስፈላጊ ፡ ያልሆነ ፡ መደጋገም ፡ ይሆናል ። ሕግ ፡ በማወጅ ፡ የሚፈጸም ፡ ማናቸውም ፡ የሕይወት ፡ የነጻነት ፡ ወይም ፡ የንብረት ፡ ማሳጣት ፡ "ሕግ" ፡ በሚለው ፡ ቃል ፡ ተራ ፡ ፍች ፡ በሕግ ፡ መሠረት ፡ የተፈጸመ ፡ ነው ። አስፈላጊ ፡ ካልሆነ ፡ መደጋገም ፡ ደረጃ ፡ ዋስትናው ፡ ከፍ ፡ የሚለው ፡ የሰውን ፡ ሕይወት ፡ ነጻነት ፡ ወይም ፡ ንብረት ፡ የሚያሳጡ ፡ ሕጎች ፡ በአንድ ፡ ከተራ ፡ ሕግ ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ሚዛን ፡ እንዲዳኙ ፡ የተፈለገ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ራሱ ፡ ተራ ፡ ሕግ ፡ የሆነው ፡ የሕዝባዊ ፡ መብቶች ፡ አዋጅ ፡ በሕግ ፡ አስገዳጅነት ፡ ሊፈጸም ፡ የሚችል ፡ ከተራ ፡ ሕግ ፡ በላይ ፡ የሆነ ፡ ሚዛን፡ ሊፈጥር ፡ እርግጥ፡ አይችልም ። አዋጁ ፡ የጠቅላላው ፡ ዓላማ ፡ መንፈስ ፡ መግለጫ ፡ ወይም ፡ የቅን ፡ ልቦና ፡ ማረጋገጫ ፡ ሆኖ ፡ መቆጠር ፡ አለበት ። ግን ፡ የአንድ ፡ መንግሥት ፡ የቅን ፡ ልቦና ፡ ማረጋገጫም ፡ ቢሆን ፡ ከተቻለ ፡ እጅግ ፡ ፍሬ ፡ ቢስ ፡ በማያደርገው ፡ አኳኋን ፡ ሊተረጐም ፡ ይገባል ።

ስለዚህ ፡ የ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ እስከ ፡ ታወጀበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ የሰውን ፡ ሕይወት ፡ ነጻነት ፡ ወይም ፡ ንብረት ፡ የሚያሳጡ ፡ እርምጃዎች ፡ ከተራ ፡ ሕግ ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ማመዛዘኛ ፡ መዳኘት ፡ ይገባቸዋል ፡ የሚለው ፡ ቀዋሚ እምነተ ፡ ሐሳብ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ በሁለት ፡ መንገድ ፡ ተዋሕዷል ፤ ይኸውም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ በኤርትራ ፡ ብቻ ፡ የሚሠራበት ፡ ቢሆን፡ ከተራ ፡ ሕግ ፡ በላይ ፡ በሆነው ፡ በፌዴራሉ ፡ ሕግ ፡ አማካይነት ፤ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ በተራ ፡ አዋጅ ፡ ሊለወጡ ፡ የሚችሉ ፡ ቢሆኑም ፡ በጠቅላላው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ሊከተሉአቸው ፡ የሚገባውን ፡ ቀዋሚ ፡ ሐሳቦች ፡ በአበሰረው ፡ በሕዝባዊ ፡ መብቶች ፡ አዋጅ ፡ አማካይነት ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ አንቀጽ ፡ ፴፫ ፡ አሁን ፡ ባሉት ፡ ሕጎች ፡ መሠረት ፡ ከመሥራት ፡ የበለጠ ፡ ዋስትና ፡ አይሰጥም ፡ የሚል ፡ ትርጉም ፤ (፩) ለአንቀጽ ፡ ፴፫ ፡ አነጋገር ፡ በብዙ ፡ ረገድ ፡ ተመሳሳይ ፡ ለሆነው ፡ ከሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ለታወጀው ፡ ለሕዝባዊ ፡ መብቶች ፡ አዋጅ ፡ ቋንቋ ፡ ከሚሰጠው ፡ ከሁሉ ፡ የበለጠ፡ ተገቢ ፡ ከሆነው ፡ ትርጉም ፡ የተለየ ፡ ፍች ፡ መስጠትን ፤ (፪) የተሻሻለው፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ከተቋቋመው ፡ ደረጃ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ እንደ ፡ አፈገፈገ ፡ አድርጎ ፡ አለማስረጃ ፡ መቀበልን ፤ ይጠይቃል ። በ(፩) ስለተመለከተው ፡ ያለው፡ አስተያየት ፡ ማናቸውም ፡ ቢሆን ፡ በ(፪) የተመለከተው ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ ከታወጀበት ፡ ግልጥ ፡ መንፈስ ፡ በርግጥ ፡ የተዛባ ፡ ነው ። [34]

---

34 ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በ፳፭ኛው ፡ የዘውድ ፡ በዓልና ፡ ተሻሽሎ ፡ የወጣውን ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ሲያውጁ ፡ ጥቅምት ፡ ፳፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ያደረጉትን ፡ የዙፋን ፡ ንግግር ፡ "ቮይስ ፡ ኦፍ ፡ ኢትዮጵያ" ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ ኖቬምብር ፡ ፲ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እትሞ ፡ ሲያወጣው ፡ እንደገለጸው ፡

"የእነዚህን ፡ ሰብአዊ ፡ መብቶች ፡ ዋስትናዎችና ፡ የሰው ፡ ልጅን ፡ መሠረታዊ ፡ ነጻነት ፡ አስፈላጊነት ፡ በመገንዘብ ፡ ተሻሽሎ ፡ በወጣው ፡ ሕገ ፡ መንግሥታችን ፡ ውስጥ ፡ እነዚህን ፡ ሰብአዊ ፡ መብቶች ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ብቻ ፡ ሳይሆኑ ፡ በተለይም ፡ እኛ ፡ እራሳችን ፡ እንድንጠብቃቸውና ፡ እንድናስከብራቸው ፡ ደንግገናል ። እነዚሁም ፡ ሰብአዊ ፡ መብቶች ፡ በማነኛውም ፡ የመንግሥት ፡ ክፍል ፡ ማለት ፡ በአስተዳደሩ ፡ ክፍል ፡ በሕግ ፡ አውጭው ፡ ክፍል ፤ ወይም ፡ በፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሊደፈሩ ፡ የማይቻሉ ፡ ዓላማዎችን ፡ የሚያጠቃልሉ ፡ በመሆናቸው ፡ በተለይ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ራሱ ፡ ሊጠብቃቸውና ፡ ሊያስከብራቸው ፡ ይገባል ። "

ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተደረገው ፡ ክርክር ፡ በአንቀጽ ፡ ፵፫ ፡ አማርኛ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ "ያለ ፡ ሕግ" ፡ የሚለውን ፡ አነጋገር ፡ ብቻ ፡ የተመለከተ ፡ ነው ። በሌሎች ፡ አንቀጾች ፡ በአማርኛውና ፡ በእንግሊዝኛው ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ ተመሳሳይ ፡ ቃላት ፡ ትርጉም ፡ እንዲሁ ፡ ተትቷል ። ሁለተኛው ፡ ክርክር ፡ ግን ፡ አንቀጽ ፡ ፵፫ን ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ እነዚህን ፡ ሌሎች ፡ አንቀጾችንም ፡ እኩል ፡ ይመለከታል ።

የሁለተኛው ፡ ክርክር ፡ መነሻ ፡ ነጥብ ፡ አንቀጽ ፡ ፷፰ ፡ ነው ፡—

"የሌሎችን ፡ ሰዎች ፡ ነጻነትና ፡ መብት ፡ ለማክበር ፤ ደግሞም ፡ የሚያስፈልገውን ፡ የሕዝብ ፡ ጸጥታና ፡ ጠቅላላ ፡ ደኅንነት ፡ ለመጠበቅ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ባሉት ፡ አንቀጾች ፡ ውስጥ ፡ መተማመኛ ፡ የተሰጣቸው ፡ መብቶች ፡ በሌላ ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ አይቀነሱም ።"

አንቀጽ ፡ ፷፰ ፡ የሕዝብ ፡ መብቶች ፡ ምዕራፍ ፡ የመጨረሻ ፡ አንቀጽ ፡ ነው ። ለያዝነው ፡ ክርክር ፡ ዋናው ፡ ጥያቄ ፡ "ያለሕግ ፡ ወይም ፡ በሕግ ፡ መሠረት" ፡ የሚልን ፡ አነጋገር ፡ የመሰሉ ፡ ሐረጎች ፡ በሚገኙባቸው ፡ አንቀጾች ፡ "ዋስትና ፡ የተሰጣቸው ፡ መብቶች" ፡ ምንድን ፡ ናቸው? በመላው ፡ አንቀጽ ፡ ከወሳኝ ፡ ሐረጎች ፡ ጋር ፡ የተገለጹት ፡ ናቸውን ፡ ወይስ ፡ እነዚህ ፡ ወሳኝ ፡ ሐረጎች ፡ ሊያሻሽሉአቸው ፡ የሚቃጡ ፡ (በገዛ ፡ ራሳቸው ፡ አነጋገር) ፡ ፍጹም ፡ የሆኑ ፡ መብቶች ፡ ናቸው ? ፍጹም ፡ የሆኑ ፡ መብቶች ፡ ከሆኑ ፡ አንቀጽ ፡ ፷፰ና ፡ ቀደም ፡ ያሉት ፡ አንቀጾች ፡ ወሳኝ ፡ ሐረጎች ፡ በሕብረት ፡ የሕዝብን ፡ የግል ፡ መብቶች ፡ መጠን ፡ የውስጥና ፡ የውጭ ፡ ወሰን ፡ የሚቆርጡ ፡ ሁነው ፡ ሊነበቡ ፡ ይቻላል ። በውጭ ፡ ወሰን ፡ ረገድ ፤ ዋስትና ፡ የተሰጣቸው ፡ መብቶች ፡ ለምሳሌ ፡ የንግግር ፡ ነጻነት ፡ በአንቀጽ ፡ ፷፰ ፡ ውስጥ ፡ የተዘረዘሩትን ፡ ተፈላጊ ፡ ነገሮች ፡ ለመጠበቅ ፡ አስፈላጊ ፡ ለሆነ ፡ አዋጅ ፡ የበታች ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ ፍጹም ፡ የሆኑ ፡ መብቶች ፡ አይደሉም ። ግን ፡ በሌላ ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ ወሰን ፤ ማለት ፡ በአንቀጽ ፡ ፷፰ ፡ ውስጥ ፡ የተዘረዘሩትን ፡ ተፈላጊ ፡ ነገሮች ፡ ለመጠበቅ ፡ ሲባል ፡ እነዚህን ፡ መብቶች ፡ የሚቀንስ ፡ ሕግ ፡ ማወጅ ፡ ማስፈለግና ፡ አለማስፈለጉ ፤ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ (ክስ ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ) ፡ ከተራ ፡ ሕግ ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ ደረጃ ፡ መሠረት ፡ መልስ ፡ የሚሰጥበት ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ የሆነ ፡ ጥያቄ ፡ ነው ። [35]

---

35 ይህ ፡ ትርጉም ፡ መሠረቱ ፡ በሕንድ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ለ፲፱ኛው ፡ አንቀጽ ፡ ከተሰጠው ፡ ትርጉም ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ሲሆን ፡ በተሻሻለው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ምዕራፍ ፡ ፫ ፡ እንደ ተደረገው ፡ የሕንድ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ምዕራፍ ፡ ፫ ፡ ውስጥ ፡ መብትን ፡ የሚወስኑ ፡ ሐረጎች ፡ ሳይኖሩበት ፡ መጀመሪያ ፡ የሕዝብ ፡ መብቶች ፡ ከዘረዘሩ ፡ በኋላ ፡ እነዚህ ፡ መብቶች ፡ ሊወሰኑ ፡ የሚችሉበትን ፡ ሁኔታ ፡ ይገልጻል ። ዲ ፡ ባሱ ፡ ኮሜንታሪ ፡ ኦን ፡ ዘ ፡ ኮንስቲቱሽን ፡ ኦፍ ፡ እንዲያ ፡ ፬ኛ ፡ እትም ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ ፲፱፻፷፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ቮልዩም ፡ ፩ ፡ ገጽ ፡ ፩፻፺፱—፺ ፡ ይመለከቷል ፤ እንዲሁም ፡ ለምሳሌ ፡ የኬንያን ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፲፱—፳፯ ፡ ይመለከቷል ።

በተባበረው ፡ የአሜሪካ ፡ መንግሥት ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ስለ ፡ ሰው ፡ መብት ፡ በፍጹም ፡ አነጋገር ፡ የተደነገገውን ፡ ለመወሰን ፡ በግልጽ ፡ የተደነገገ ፡ ነገር ፡ ባይኖርም ፡ የፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ትርጉም ፡ ከአንቀጽ ፡ ፷፰ ፡ ጋር ፡ ተመሳሳይ ፡ የሆነ ፡ ውጤት ፡ ለማስገኘት ፡ ችሏል ፡ ለምሳሌ ፡ ሼንክ ፡ ከዩናይትድ ፡ እስቴትስ ፡ ጋር ፡ በጠቅላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ (፲፱፻፲፱ ፡ እ ፡ እ ፡ አ ፡) በተካሰሱበት ፡ ክርክር፡ ዩ ፡ ኤስ ፡ ሪፖርት ፡ ቮል ፡ ፪፻፵፱ ፡ ገጽ ፡ ፵፯ ፡ ፶፩ ፡ ሎውየርስ ፡ ኤድ ፡ ቮል ፡ ፷፫ ፡ ገጽ ፡ ፩፻፸ ፡ ፩፻፸፬ ፡ ሆልምስ ፡ ጂ ፡ የንግግርን ፡ ነጻነት ፡ በሰፊው ፡ የሚጠብቅ ፡ ሕግ ፡ በትያትር ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ እሳት ፡ ተነሣ ፡ ብሎ ፡ በውሸት ፡ በመጮህ ፡ በተመልካቾች ፡ ዘንድ ፡ ፍርሐትና ፡ ሽብር ፡ የፈጠረውን ፡ ሰው ፡ አይደግፍም ፡ ያለውን ፡ ይመለከቷል ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ ለተገለጸው ፡ ፍች ፡ ያለው ፡ ድጋፍ ፡ ከእርግጠኛነቱ ፡ ይበልጥ ፡ መጠኑ ፡ ብዙና ፡ የተለያየ ፡ ነው ። ቢሆንም ፡ ፍችውን ፡ በቁም ፡ ነገር ፡ ሊታይ ፡ የሚገባው ፡ ሌላ ፡ መንገድ ፡ አድርጎ ፡ ለማስቀጠር ፡ ብቁ ፡ የሆነ ፡ ድጋፍ ፡ ይመስላል ። አንደኛ ፡ ተመሳሳይ ፡ ለሆኑ ፡ የኤርትራ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጾች ፡ በዳኝነት ፡ የተሰጣቸው ፡ ፍች ፡ አለ ። ኤርትራ ፡ በፌዴራሲዮን ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ስትቀላቀል ፡ የወሰደችው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ከአንቀጽ ፡ ፳፫ ፡ ጋር ፡ በብዙ ፡ ረገድ ፡ አንድ ፡ የሆነ ፡ አንቀጽ ፡ ይዟል ። ከዚህም ፡ በላይ ፡ በኤርትራ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ከተሰጡት ፡ የሕዝብ ፡ መብቶች ፡ አንዱ ፡ ማንኛውንም ፡ ሥራ ፡ እየሠሩ ፡ የመኖር ፡ መብት ፡ "ሕግ ፡ በሚያዘው ፡ መሠረት" ፡ በሚል ፡ ወሳኝ ፡ ሐረግ ፡ የተወሰነ ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ አሁን ፡ በአንቀጽ ፡ ፳፫ ፡ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ምዕራፍ ፡ ፫ ፡ የመጀመሪያዎቹ ፡ አንቀጾች ፡ የቀረበው ፡ ያው ፡ የአተረጓጐም ፡ ጥያቄ ፡ ተደቅኖ ፡ ነበር ፤ ወሳኙ ፡ ሐረግ ፡ ሕገ፡ መንግሥታዊ፡ የሆኑ፡ መብቶችን፡ የሕጎች፡ ሁሉ ፡ በታች ፡ ያደርጋቸዋልን? ወይስ ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ ደረጃን ፡ ከጠበቁ ፡ ሕጎች ፡ ብቻ ፡ በታች ፡ ያደርጋቸዋል ?

በ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በተሰጠ ፡ ብይን ፡ የኤርትራ ፡ ጠቅላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የኋለኛውን ፡ መንገድ ፡ መርጧል ። ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ውሳኔ ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ ሕግ ፡ ጥሳችኋል ፡ በመባል ፡ የተፈረደባቸውን ፡ ሰዎች ፡ ከጥብቅና ፡ ሥራ ፡ ያገደ ፡ አንድ ፡ የኤርትራ ፡ አዋጅን ፡ [37] ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ መሆን ፡ በመቃወም ፡ የቀረበ ፡ ይግባኝ ፡ ነው ። ማነኛውንም ፡ ሥራ ፡ የመሥራት ፡ መብት ፡ አጋጊው ፡ በሚያወጣው ፡ ማናቸውም ፡ ሕግ ፡ ተጠያቂ ፡ ከሆነ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ማናቸውም ፡ ሕግ ፤ ኢሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ (ሕገ ፡ መንግሥታዊ)፡ ያልሆነ ፡ ሊሆን ፡ እንደማይችል ፡ ግልጽ ፡ ነው። ይሁን፡ እንጂ፡ ፍርድ፡ ቤቱ፡ አነስተኛ፡ በሆነ፡ ጥፋት ፡ ብቻ ፡ ጥፋተኛ ፡ ሆኖ ፡ መገኘትን ፡ ይዞ ፡ በቀረበለት ፡ በዚያ ፡ ጉዳይ ፡ ረገድ ፡ አዋጅ ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ አይደለም ፡ ሲል ፡ በይኗል ። "ሕግ ፡ በሚያዘው ፡ መሠረት" ፡ የሚለው ፡ ወሳኝ ፡ ሐረግ ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ የሆነን ፡ መብት ፡ "የሌሎችን ፡ ሰዎች ፡ ነጻነትና ፡ መብት ፡ ለማክበር ፤ ደግሞም ፡ የሚያስፈልገውን ፡ የሕዝብ ፡ ጸጥታና ፡ ጠቅላላ ፡ ደህንነት ፡ ለመጠበቅ" ፡ ሲባል ፡ አስፈላጊ ፡ ከሆኑ ፡ ሕጎች ፡ ብቻ ፡ በታች፡ ያደርጋቸዋል ፡ ተብሏል ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ አስፈላጊ ፡ ያልሆነ ፡ ሕግ ፡ ከሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ መብት ፡ ጋር ፡ በተጋጨበት ፡ መጠን ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ይሆናል ።

ለአንቀጽ ፡ ፳፫ና ፡ ለምዕራፍ ፡ ፫ ፡ የሕዝብ ፡ መብቶች ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ለተሰጣቸው ፡ ፍች ፡ ሁለተኛ ፡ ድጋፍ ፡ የሚሆነው ፡ የአመጣጣቸው ፡ ታሪክ ፡ ነው ። በግልጽ ፡ ባይሆንም ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ አሳሰብነው ፡ አንቀጽ ፡ ፳፫ ፡ ራሱ ፡ ተመሳሳይ ፡ ቋንቋ ፡ ይዞ ፡ ከሚገኘው ፡ ከኤርትራው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ወይም ፡ ከፌዴራሉ ፡ ሕግ ፡ የተወረሰ ፡ ይመስላል ። ሕግ ፡ በሚያዘው ፡ መሠረት ፡ የሚል ፡ አነጋገር ፡ ተጠቅሶ ፡ ሳይወሰኑ ፤ የኤርትራው ፡ ሕገ ፡ መንግሥትና ፡ የፌዴራሉ ፡

---

36 ሁለቱም ፡ ድንጋጌዎች ፡ እላይ ፡ በ፩ኛ ፡ የግርጌ ፡ ማስረጃ ፡ ከተጠቀሰው ፡ የፌዴራል ፡ ሕግ ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ የተወሰዱ ፡ ናቸው ። ከሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፳፭ ፡ ጋር ፡ ተመሳሳይ ፡ የሆነው ፡ የፌዴራል ፡ ሕግ ፡ የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ በ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ያስተላለፈውን ፡ ዩኒቨርሳል ፡ ዲክለሬሽን ፡ ኦፍ ፡ ሁመን ፡ ራይትስ ፡ አንቀጽ ፡ ፳፱ ፡ (፪) በመጠኑ ፡ በማሻሻል ፡ የተወሰደ ፡ ነው ።

37 ውሳኔው ፡ ለሕዝብ ፡ ታትሞ ፡ አልወጣም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አስተዋጽኦውን ፡ ጂ ፡ እስሚዝ ፡ "ሂውመን ፡ ራይትስ ፡ ኢን ፡ ኤርትራ" ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ በሞደርን ፡ ሎው ፡ ሪቪው ፡ ቮልዩም ፡ ፲፳/፲፱፻፶፩ ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ ገጽ ፡ ፬፻፹፬-፬፻፹፮ ፡ ጽፎአል ፡ ላሁኑ ፡ ጽሑፉችን ፡ መሠረት ፡ ያደረግነው ፡ ይህንኑ ፡ አስተዋጽኦ ፡ ነው ።

ሕግም ፡ ብዙዎቹን ፡ የምዕራፍ ፡ ፫ ፡ የሕዝብ ፡ መብቶች ፡ የሃይማኖት ፡ የንግግርና ፡ የማኅበር ፡ አባልነት ፡ ነጻነት ፡ ዋስትናዎችም ፡ ሳይቀሩ ፡ ይዘዋል ። ስለዚህ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ማናቸውንም ፡ ዓይነት ፡ ሥራ ፡ እየሠሩ ፡ ስለመኖር ፡ መብት ፡ በኤርትራ ፡ ጠቅላይ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ በተሰጠው ፡ ፍች ፡ ቢስማማም ፡ ባይስማማ ፡ "በሕግ ፡ መሠረት" ፡ የሚል ፡ አነጋገር ፡ ባልተጠቀሰባቸው ፡ መብቶች ፡ ላይ ፡ ፍችውን ፡ እንዲቀበል ፡ ይገደዳል ። ስለዚህም ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ስለ ፡ አንቀጽ ፡ ፵፫ ፡ ብቻ ፡ ተፈጥሮ ፡ ወደ ፡ ነበረው ፡ የነገር ፡ ስንጠራ ፡ (ክፈላ) ፡ ይመራል ። አንድም ፡ እንደ ፡ "በሕግ ፡ መሠረት" ፡ ያሉ ፡ ወሳኝ ፡ ሐረጎች ፡ "በአንቀጽ ፡ ፳፭ ፡ ውስጥ ፡ የተዘረዘሩትን ፡ ዐቢይ ፡ ፍላጎቶች ፡ ለመጠበቂያ ፡ በሚያስፈልጉት ፡ ሕጎች ፡ መሠረት "፡ ማለታቸው ፡ ነው ፡ ተብለው ፡ ይነበባሉ ፤ አለበለዚያም ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ የሕዝብን ፡ መብቶች ፡ በሚነካ ፡ ነገር ፡ በፌዴራሉ ፡ ሕግና ፡ በኤርትራ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ከተቋቋመው ፡ ደረጃ ፡ በጣም ፡ ዝቅ ፡ ብሏል ። [38]

ሦስተኛ ፡ በመጨረሻም ፡ ጉዳዩ ፡ የሚመለከታቸውን ፡ አንቀጾች ፡ ዋጋ ፡ የሚያሳጣ ፡ ፍች ፡ መቀበልን ፡ የሚደግፍ ፡ እምነት ፡ አለ ። በምዕራፍ ፡ ሦስት ፡ ለሚገኙ ፡ ሌሎች ፡ አንቀጾች ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ፍች ፡ ቢሰጥ ፡ አንቀጽ ፡ ፳፭ ፡ ራሱ ፡ ቀደም ፡ ብለው ፡ ቀርበው ፡ የነበሩትን ፡ ሁለት ፡ መሠረታዊ ፡ ዓላማዎች ፡ ማለት ፡ በተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ የተሰጡት ፡ የሕዝብ ፡ መብቶች ፡ ሌሎች ፡ ዐቢይ ፡ ፍላጎቶችን ፡ ለመጠበቅ ፡ ሲባል ፡ ሊወሰኑ ፡ እንደሚችሉ ፡ በሌላ ፡ ምክንያት ፡ ግን ፡ ሊወሰኑ ፡ እንደማይችሉ ፡ የሚለውን ፡ መሠረተ ፡ ሐሳብ ፡ እንዲያቋቁም ፡ የተፈለገ ፡ ይመስላል ። እንደ ፡ "በሕግ ፡ መሠረት" ፡ ዓይነቱ ፡ ወሳኝ ፡ ሐረግ ፡ ሐረጉ ፡ የሚገኝባቸውን ፡ መብቶች ፡ ከሕጎች ፡ ሁሉ ፡ በታች ፡ ያደርጋቸዋል ፡ ማለት ፡ ከሆነ ፡ አንቀጽ ፡ ፳፭ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ዓላማው ፡ የሚያስፈልግ ፡ ሁለተኛ ፡ ዓላማውንም ፡ ለመፈጸም ፡ የማይችል ፡ ነው ። መብቶቹ ፡ ከማንኛውም ፡ አዋጅ ፡ በታች ፡ ከሆኑ ፡

---

38 ተሻሽሎ ፡ የወጣው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ የኤርትራ ፡ ሕገ ፡ መንግሥትን ፡ ያህል ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ መብት ፡ የማይሰጥ ፡ ከሆነ ፡ የኤርትራ ፡ ሕዝብ ፡ የተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ከመውጣቱ ፡ በፊት ፡ ከነበራቸው ፡ መብት ፡ ተቀንሶባቸዋል ፡ ብሎ ፡ ለመከራከር ፡ ይቻላል ፤ የዚህንም ፡ ክርክር ፡ ትክክል ፡ መሆን ፡ አለመሆን ፡ ለማረጋገጥ ፡ የኢትዮጵያና ፡ የኤርትራን ፡ ፌዴሬሽን ፡ በመሰረዝ ፡ ኤርትራ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጋር ፡ በአንድነት ፡ እንድትዋሐድ ፡ ያደረገው ፡ በ፲፱፻፶፭ኛው ፡ ዓመት ፡ ቍጥር ፡ ፫ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ የወጣው ፡ ፳፯ኛ ፡ ትእዛዝ ፡ በፌዴራሉ ፡ አዋጅና ፡ በኤርትራ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ የሚያስከትለውን ፡ ውጤት ፡ መመርመር ፡ ያሻል ። ይህ ፡ ትእዛዝ ፡ በአንቀጽ ፡ ፬ ፡ እስከ ፡ ፮ ፡ በሚያትተው ፡ መሠረት ፡ አብዛኛዎቹን ፡ ነባር ፡ የኤርትራ ፡ ሕጎች ፡ ሳይለውጥ ፡ ትቷል ፤ ለማለት ፡ ይቻል ፡ ይሆናል ። አንቀጾችም ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ።

"ቍ.፬፤ማናቸውም ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ወይም ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ የሰውነት ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ ድርጅት ፡ በሕግ ፡ በትእዛዝ ፡ በውል ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ አኳኋን ፡ በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ የተፈቀደለት ፡ የተሰጡት ፤ ወይም ፡ ያገኛቸው ፡ ማናቸውም ፡ መብቶች ፤ ከግዴታዎች ፡ ነጻ ፡ የሚያደርጉ ፡ መብቶች ፤ ከንሴሲዮኖችና ፡ ልዩ ፡ መብቶች ፤ እንዲሁም ፡ የማይንቀሳቀስ ፡ ንብረትን ፡ የማግኘት ፤ ባለቤት ፡ የመሆን ፤ ባለቤትነትን ፡ የማስተላለፍ ፡ መብቶች ፡ ጭምር ፡ እንዳሉ ፡ በሙሉ ፡ ጸንተው ፡ ይቀጥላሉ ።

ቍ.፭፤የቀድሞ ፡ የኤርትራ ፡ አስተዳደር ፤ ሥልጣኖች ፤ ተግባሮችና ፡ ግዴታዎች ፡ የነበሩት ፡ ሁሉ ፡ በዚህ ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ መብቶች ፤ ሥልጣኖች ፤ ተግባሮች ፡ ግዴታዎች ፡ ሆነዋል ።

ቍ.፮፤ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ በኤርትራ ፡ ውስጥ ፡ ጸንተው ፡ የሚሠራባቸው ፡ ወይም ፡ የፌዴራል ፡ አቋም ፡ በመኖሩ ፡ ምክንያት ፡ የወጡት ፡ ሕጎች ፤ አዋጆችና ፡ ደንቦች ፡ በሙሉም ፡ ሆነ ፡ በከፊል ፤ ለአስተዳደሩ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆነው ፡ እንዲሠራባቸው ፡ የሚያስፈልጉት ፡ ሁሉ ፡ ወደፊት ፡ በሚወጡ ፡ ሕጎች ፡ ተሠርዘው ፡ እስኪተኩ ፡ ድረስ ፡ እንዳሉ ፡ ጸንተው ፡ የሚሠራባቸው ፡ ይሆናሉ ። ያሉትም ፡ የአስተዳደር ፡ ድርጅቶች ፡ በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ሆነው ፡ እነዚህኑ ፡ ሕጎች ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ መዋላቸውን ፡ እንዲቀጥሉ ፡ ያደርጋሉ ።"

መብቶች ፡ ሊወሰኑ ፡ መቻላቸውን ፡ በአንቀጽ ፡ ፷፭ ፡ ማረጋገጥ ፡ አያሻም ። እንዲ ህም ፡ ከሆነ ፡ በአንዳንድ ፡ ምክንያት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ መብቶች ፡ አይወሰኑም ፡ የሚል ፡ ዋስትና ፡ ስሜት ፡ የማይሰጥ ፡ ነው ።

በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ የተባሉት ፡ ዓይነት ፡ ወሳኝ ፡ ሐረጎች ፡ በማይገኙባ ቸው ፡ አንቀጾች ፡ ረገድ ፡ ትርጉም ፡ የሚያጣው ፡ አሁን ፡ ያቀረብነው ፡ ፍች ፡ ነው ። እነዚህም ፡ አንቀጾች ፡ በምዕራፍ ፡ ፫ ፡ ውስጥ ፡ ቍጥራቸው ፡ ያየለ ፡ ነው ። ከአን ቀጽ ፡ ፷፭ ፡ በቀር ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ውስጥ ፡ መብቶችን ፡ ለሕዝብ ፡ ለመስጠት ፡ ከሚቃጡት ፡ ሀያ ፡ ስድስት ፡ አንቀጾች ፡ ዘጠኙ ፡ ብቻ ፡ በእንዲህ ፡ ዓይነቱ ፡ አነ ጋገር ፡ ተወስነዋል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ አንቀጽ ፡ ፷፭ን ፡ በአረቀቀው ፡ ሰው ፡ ሐሳብ ፡ ውስጥ ፡ ነበሩ ፡ ተብለው ፡ ሊገመቱ ፡ የሚቻሉት ፡ እነዚህ ፡ "በሕግ ፡ መሠረት" ፡ በሚል ፡ ዓይነት ፡ አነጋገር ፡ የተወሰኑት ፡ ማለት ፡ አንቀጽ ፡ ፵፩ና ፡ የንግግር ፡ የሃይ ማኖት ፡ የስብሰባና ፡ የማኅበር ፡ ነጻነት ፡ ዋስትናዎች ፡ የሆኑት ፡ አንቀጾች ፡ ናቸው ። አንቀጽ ፡ ፷፭ ፡ በነዚህ ፡ አንቀጾች ፡ አግባቡ ፡ ትርጉም ፡ ከሌለው ፡ በጠቅላላው ፡ ሊኖረው ፡ የሚችለው ፡ ትርጉም ፡ እምብዛም ፡ ነው ።

## መደምደሚያ ።

የዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፤ ማለት ፡ ሕይወትን ፡ ነጻነትን ፡ ወይም ፡ ንብረ ትን ፡ ለማሳጣት ፡ የሚያሰጋ ፡ የመንግሥት ፡ የአስተዳደር ፡ አድራጎት ፡ በአዋጅ ፡ የተፈቀደ ፡ ቢሆንም ፡ በዳኝነት ፡ እንደገና ፡ እንዲታይ ፡ በተገቢ ፡ የሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ዋስትና ፡ (ማለት ፡ በአንቀጽ ፡ ፵፫) ፡ የተጠበቀ ፡ መሆን ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ክርክር ፡ ያልተደረገበት ፡ ጉዳይ ፡ ነው ። ክርክር ፡ የተደረገባቸው ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ነጥቦች ፡ በሁሉም ፡ ወይም ፡ በጥቂቶቹ ፡ ጉዳዮች ፡ ውስጥ ፡ ለዚሁ ፡ ጥያቄ ፡ እንደ ፡ መነሻ ፡ ሐሳቦች ፡ የሚሆኑ ፡ ናቸው ። ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ አይደሉም ፡ የተባሉ ፡ የአዋጅ ፡ ትእዛዞችን ፡ ለመሻር ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሥልጣን ፡ ካልኖራቸው ፡ ወይም ፡ አንቀጽ ፡ ፵፫ ፡ ሕገ ፡ መንግሥታዊ ፡ የሆነ ፡ የሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ደረጃ ፡ የማይፈጥር ፡ ከሆነ ፡ አንድ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እዚህ ፡ በአሳሰብነው ፡ ዓይነት ፡ ሁናቴ ፡ የተገቢ ፡ የሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ፍላጎት ፡ የሚሰነዝረውን ፡ ሐሳብ ፡ ለመመርመር ፡ በም ንም ፡ አኳኋን ፡ ዕድል ፡ አይገጥመውም ። የአንቀጽ ፡ ፻፳፪ ፡ ወደፊት ፡ በሚሠሩ ፡ የመንግሥት ፡ አድራጎቶች ፡ ብቻ ፡ መወሰን ፡ ፍች ፡ ጉዳይ ፡ ግን ፡ አድራጎቱ ፡ በተ ፈጸመበት ፡ ቀን ፡ መሠረት ፡ በአንድ ፡ የተለየ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ሊነሣ ፡ ወይም ፡ ላይ ነሣ ፡ ይችል ፡ ይሆናል ። በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ አንቀጽ ፡ ፻፳፪ም ፡ ጉዳዩን ፡ ሌላ ፡ እርምጃ ፡ ሳይወሰድ ፡ ይግባኙን ፡ ባለመቀበል ፡ ለመወሰን ፡ ያስችላል ። የነዚህ ፡ ጥያቄዎች ፡ አቀራረብ ፡ በአስተዳደር ፡ በሚፈጸሙ ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ አድራጎቶች ፡ አራሚነት ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ሰፊ ፡ ሥልጣን ፡ እንዲኖራቸው ፡ የሚደግፉትን ፡ የደራሲውን ፡ እምነት ፡ ያለጥርጥር ፡ ያሳያል ። ለተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በዳኝነት ፡ የሚሰጠው ፡ ፍች ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ የበላይ ፡ ሕግ ፡ መሆ ኑንና ፤ የአስተዳደር ፡ አድራጎቶችን ፡ በዳኝነት ፡ እንደገና ፡ ከመታየት ፡ የሚከለ ክል ፡ አዋጅም ፡ ከተሻሻለው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ በላይ ፡ መሆን ፡ በራሱ ፡ በዳኝ ነት ፡ እንደገና ፡ ማየትን ፡ ማገድ ፡ እንደማይገባው ፤ ከፍ ፡ ብሎ ፡ ክርክር ፡ ተደር ጎበታል ። እንዲሁም ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ የአንቀጽ ፡ ፵፫ ፡ የቋንቋ ፡ ችግር ፡ ምር ምር ፡ አንድ ፡ ማጠቃለያ ፡ ሐሳብ ፡ ከውስጡ ፡ እንዲወጣ ፡ ለማድረግ ፡ በሚበቃ ፡ ያልተሟላ ፡ ቢሆን ፡ አንቀጽ ፡ ፵፫ ፡ ተገቢ ፡ የሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓትን ፡ ለመሰለ ፡ ነገር ፡ ዋስትና ፡ መስጠቱን ፡ የሚደግፉ ፡ ሁለት ፡ ዓይነት ፡ ክርክሮች ፡ ቀርበዋል ።

ስለ ፡ መጀመሪያዎቹ ፡ ሁለት ፡ አከራካሪ ፡ ጉዳዮች ፡ የተሰጠው ፡ ማጠቃለያ ፡ ሐሳብና ፡ ስለ ፡ ሦስተኛው ፡ አከራካሪ ፡ ጉዳይ ፡ የተሰጠው ፡ የክርክር ፡ አቅጣጫ ፡ ተቀባይ ፡ ያገኙ ፡ እንደሆን ፤ ተገቢ ፡ የሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ (ማለት ፡ አንቀጽ ፡ ፴፯) ፡ በኢትዮጵያ ፡ የአሠራር ፡ አግባቡ ፡ ዳኝነት ፡ እንደገና ፡ የማየትን ፡ መብት ፡ መያዝ ፡ የሚገባው ፡ መሆን ፡ ገና ፡ በአንድ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ እስኪወሰን ፡ የሚጠብቅ ፡ ነው ። ይህ ፡ ጉዳይ ፡ የተወሳሰበ ፡ ነው ። በመጨረሻም ፡ በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ የሚገለጸው ፡ ጉዳዩ ፡ በነጠላ ፡ ጥያቄ ፡ መቅረቡ ፡ አንድ ፡ መልስ ፡ ብቻ ፡ ሊሰጠው ፡ ይገባል ፡ ለማለት ፡ አለመሆኑ ፡ ነው ። ለአንዱ ፡ ዓይነት ፡ የመንግሥት ፡ የአስተዳደር ፡ አድራጎት ፡ የሚሰጠው ፡ መልስ ፡ ለሌላው ፡ እንደሚሰጠው ፡ መልስ ፡ መሆን ፡ አይገባው ፡ ይሆናል ። ምናልባትም ፡ ስለ ፡ ማናቸውም ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ የመንግሥት ፡ አድራጎት ፡ የሚሰጠው ፡ መልስ ፡ በዳኝነት ፡ እንደገና ፡ እንዲታይ ፡ በተጠየቀው ፡ ጭብጥ ፡ መሠረት ፡ ሊለያይ ፡ ይገባው ፡ ይሆናል ።